ለእስልምና እምነት ተከታዮች ዒድ ሙባረክ እንዲሁም ለክርስትና እምነት ተከታዮች እናኳን ለብርሀነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ



ኤርትራ
የዓለማችን ቁጥር
አንድ ጋዜጠኞች
የሚታጎሩባት
አገር ተባለች

13



ለአህጉር አፍሪካ
ከመከራከር፣ ቆቃ
ኃይቅን የመታደግ
ቤት ሥራ ይቅደም!
በፕሮፌሰር
አለማየሁ ገ/ማርያም

3



ኃይሌ ገ/ሥላሴ ዳግም
በበርሊን ነገሰ!

14


# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ


2ኛ ዓመት ቁጥር 82 | መስከረም 12 ቀን 2002 | ዋጋ 3.50 ብር


## የአፋር ክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ዋሉ

**5** የኮንስትራክሽን ሎደር እና ትራክተሮች

**4** ገልባጭ መኪኖች

**6** የቤት አውቶሞቢሎች



እና የተለያዩ ዘመናዊ ቤቶች ጥቆማ ቀርቦባቸዋል

13

## ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ ለ ጠ/ሚ መለስ ምላሽ ሰጠ



በቅርቡ የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓትን እና ያስከተለውን ውጤት አስመልክቶ ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ የተባለ ዓለም አቀፍ ተቋም «Ethiopia: Ethnic Federalism and its Discontents» በሚል ርዕስ የኢትዮጵያን መንግስት የሚተች ሪፖርት ማውጣቱ ይታወሳል። ተቋሙ ባወጣው ሪፖርት በኢትዮጵያ እየጨመረ በመጣው የብሔር ውጥረቶች እና ልዩነቶች አማካኝነት ግጭት ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ጠቁሟል። ይህንን አስመልክቶም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም በጽ/ቤታቸው ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ውይይት ተቋሙ ከኤርትራ ጋር በቅርብ እንደሚሰራ ጠቅሰው «የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ» ሲሉ ሪፖርቱን ተችተውት ነበር። የኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ የአፍሪካ ጉዳዮች ምክትል ዳይሬክተር የሆኑት ዳንኤል ክርስለስ ባሳለፍነው ሳምንት ለጠ/ሚ/ሩ ትችት ምላሽ መስጠታቸው ታውቋል።

ተቋሙን ከሚያንቀሳቅሰው የገንዘብ ምንጭ ጋር በማያያዝና ከዚህ ቀደም በተለያዩ ሀገራት ለምን ዓይነት ተግባሮች እንደዋለ በማስታወስ የሪፖርቱን ሚዛናዊነት የነቀፉት አቶ መለስ የአፍሪካ ቀንድን በተመለከተ የተቋሙን ሥራ የሚሰራው በአንድ ወቅት የኤርትራ መንግስት አምባሳደር የነበሩ ግለሰብ መሆኑንም ገልጸው ነበር። ይሁንና ግን ምክትል ዳይሬክተሯ ለአሜሪካ ድምጽ ጋዜጠኛ ለትዝታ በላቸው እንደገለፁት የተቋሙ ሠራተኛ የነበረው ኤርትራዊ ግለሰብ ከዓመት በፊት ከተቋሙ መልቀቁንና ይህንንም ሪፖርት አለማዘጋጀቱን ጠቁመው በሪፖርቱ ላይ ምንም ዓይነት የኤርትራ ተሳትፎ አለመኖሩን አስታውቀዋል።

ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ እንደዚህ መሳዩ ብዙም እንዳላስገረማቸው በጋዜጣዊ መግለጫው ወቅት የተናገሩት አቶ መለስ «ከበስተጀርባ ትልቅ ባለሀብት አለ። ትርፍ ገንዘብ ያለው ትልቅ ባለሀብት፤ እናም በትርፍ ገንዘብ አማካኝነት የፖለቲካ ቁም ነገር ለመስራት የሚፈልግ። ያ ቁምነገር ግን እኛ ቁም ነገር ብለን በምንፈርጀው መልኩ አይደለም።» ብለው ነበር።

ወደ ገፅ 13 ዞሯል



ለመድረክ የቀረበለት የድርድር ቀነ ገደብ
የፊታችን አርብ ያበቃል

13




13

# ኤዲቶሪያል

## «የዴሞክራሲ ቀን»ን ለማክበር የሞራል ስንቅ የሚሆኑንን ግብአቶች እናሟላ!

በጀመርነው የ2002 ዓ.ም መባቻ በአለም አቀፍ ደረጃ የደሞክራሲ ቀን ተከብሮ ውሏል:: መሪ ቃሉም «ዴሞክራሲ እና ፓለቲካዊ መቻቻል» የሚል ነበር:: በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ከሁለት አመት በፊት በየአመቱ እንዲከበር የተደረገውን ይህን አለም አቀፍ ክብረ በዓል አገራችንም አክብራ መዋሏን የመገናኛ ብዙሃን ገልፀዋል:: «ሕዝባዊ አስተዳደር» የሚል ትርጓሜ ያለው ይህ የስርአት ቅርጽ የተከበረበት ምክንያት ጽንሰ ሃሳቡን ለማስረጽ የማስተዋወቂያ አጋጣሚ እንዲሆንና በሌላ በኩልም የአስተዳደር ስርአቱ እውን ሆኖ እንዲሰፍን ለሰው ልጆች የሚያጎናጽፋቸውን በረከቶች ለማወደስ የሚል ነውና:: ተገቢና ቅዱስ ተግባር ነው ብለን እናምናለን:: ይሁንና የዴሞክራሲ ስርአት ማስፈን እለቱን አክብሮ የመዋልን ያህል የቀለለና የጽንሰ ሃሳቡን አንድምታዎች ባሸበረቁ ቃላት የማቀንቀን ያህል የዋዛ ያለመሆኑን የምንገነዘብበት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ እንገኛለን::

«ዴሞክራሲ» የተፀነሰው ከ7500 አመታት በፊት ቢሆንም የተጓዘባቸው እጅግ ረዥም የጊዜ ምዕራፎች ግን አዝጋሚና እድገቱን ከሚያኮላሹ የፖለቲካ መሪዎች ብርቱ መዳፍ ስር መውጣት ያለመቻሉን የሚያመለክቱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መገለጫዎች አሉት:: የስርአቱ መገለጫዎች ምንድናቸው? በስርአቱ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ አገራት ከጽንሰ ሀሳቡ ጋር ተስማምተው የሚጓዙበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃርስ የገዢው ፓርቲና የተፎካካሪ ፓርቲዎች አይነተኛ ድርሻ፣ የሲቪል ማሕበራት፣ የህግና የፍትህ መዋቅሩ፣መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የዜጎች የአስተዋጽኦ መስተጋብር ምን ይመስላል? የሚለውን ግድ ይላል::

በዘመናችን እየተሰራበት የሚገኘው «የውክልና ዴሞክራሲ» ዜጎች ይወክሉኛል፣ ይመሩኛል የሚሏቸውን ግለሰቦች ከመካከላቸው በመምረጥ ለስልጣን የሚያበቁበት ስርአት እንደሆነ ይታወቃል:: ስርአቱ ዜጎች በድምፃቸው ለስልጣን ያበቋቸውን ወኪሎች ትግበራ በመከታተል ብቃት ያላቸው (የሕዝቡን ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶች እስከተቻለው ደረጃ ድረስ የሚያደርሱ) ከሆኑ የውክልና ጊዜያቸው ከተጠናቀቀም በኋላ በድጋሚ የሚመርጥበት (ህጉ በሚደነግገው መሰረት)፣ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ከሆነ ደግሞ ከወቅቱ ቀደም በማለት የሚያነሳበት ስርአት ነው:: (የብዙሃን ፍላጎት የአናሳዎችን ህገ መንግስታዊ መብት ጥበቃዎች በማክበር ተፈፃሚ የሚሆንበት የአብላጫ ድምጽ አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ) በአገራችን ለሁነቱ የነበረው ልማዳዊ ትግበራና ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል? ምን ማድረግስ ይጠበቅብናል?

አገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ለሚሸፍናቸው ክንውኖችና ድርጊቶች አዲስ አይደለችም:: ከበርካታ መቶ አመታት በፊት ጀምሮ ማህበራዊ ግብይቶችን ለማከናወን ከሕብረተሰቡ ውስጥ በስነ ምግባራቸው፣ በእውቀታቸውና በልምዳቸው የሚመረጡ ግለሰቦች ማህበራዊ ምጣኔ ሃብታዊና

ፖለቲካዊ ተግባራትን እንዲያከናወኑ ይሾሙ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ታሪክ ስንመረምር የብዙሃንን ድጋፍ በማግኘታቸው ተሾመው የተጣለባቸውን ኃላፊነት ይወጡ የነበረበት አሰራር እንደነበር መረዳት እንችላለን፡፡ ሰፊ የሕዝብ ቁጥር ያለው የኦሮሞ ህዝብ ይተዳደርበት የነበረውን የገዳ ስርአት በምሳሌነት ብናነሳ ሁኔታውን ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል፡፡

በገዳ ስርአት ውስጥ በየስምንት አመቱ ይደረግ የነበረው የስልጣን ሹም ሽር ልሂቃን ይመረጡ የነበረው ባላቸው ተቀባይነት፣ ችሎታና ብቃት ብቻ ሲሆን አመራረጡም ፍፁም ዴሞክራሲያዊ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያረጋግጣሉ፡፡ በብቃታቸው ብቻ የሚመረጡት ግለሰቦች ኃላፊነታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ሳይወጡ ቢቀሩም በድምፁ ለስልጣን ያበቃቸው ህዝብ ከኃላፊነታቸው የሚያነሳበት «ቡቂሱ» (ከቦታው ላይ ማንሳት የሚል ትርጉም አለው) የሚባል ስርአት ነበረው፡፡ ከተረኛው የገዳ ስር ሌላ ሰው ተመርጦ የውክልና ጊዜው እንዲጠናቀቅ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ የአገራችንን የሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ባህላዊ የአስተዳደር ስርአቶች ብንመረምር ዴሞክራሲያዊ አሰራር ለኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ አመታት የተዋወቀ የጽንሰ ሃሳብ ትግበራ እንዳልሆነ ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን፡፡ ይሁንና የዴሞክራሲ ቀን በሚከበርበት የዓመታት ጉዞ ማግስት እንኳ የስርአቱን ትውፊቶች መቋደስ ያለመቻላችን አሳሳቢና ችግሩ ምንድነው? መፍትሔውስ? በሚለው ላይ እንድንወያይ የሚያደርግ ነው፡፡

በእኛ እምነት «ዴሞክራሲ እና የፖለቲካ መቻቻል» በሚል ባለፈው ሳምንት የተከበረው ዓለም አቀፍ ቀን በመግቢያችን ላይ የተመለከትናቸውንና በዘመን ሽግግር እስከዛሬ ያልሰራናቸውን የቤት ስራዎች ቆም ብለን ማጠናቀቅ እንዳለብን የሚያሳስቡ ናቸው፡፡ በገዢው ፓርቲ፣ በተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ በሲቪል ማሕበራት፣ በሕግና የፍትህ መዋቅሮች፣ በሚዲያው እና በግለሰብ ደረጃ በዜጎች ጫንቃ ላይ የተጣለ ታሪካዊ የቤት ሥራዎች ናቸው፡፡ አዎ! ከተጠያቂነት ባፈነገጠ ዓለም አቀፍ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን ከመቀበል ይልቅ ልንወጣው ባልቻልነው የድህነትና የመልካም አስተዳደር እጦት ሽክርክሪት ውስጥ ሆነን «ለዓለም ዴሞክራሲን እናስተምራለን» ስንል እውነታውን መደፍጠጥና መራር ስላቅ ይሆንብናልና፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ካለፉት 20 ዓመታት አካባቢ ወዲህ በየአምስት አመቱ የተለያዩ ዘርፎች ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችንና ሲያራምድ የቆየ ሲሆን የያዝነው አመት አገር አቀፍ ምርጫ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ባልታወቀበት ሁኔታ ስለቀጣዮቹ አምስት የስልጣን አመታት ጠ/ሚ/ሩ ማን መሆን እንዳለበት በማመት የቤት ሥራ ተወጥሮ እየተመለከትን ነው፡፡ (ምንም እንኳን ለአሁኑ ምርጫ መፎካከር የሚችሉ ፓርቲዎች ባይኖሩም) የዚህን ሁኔታ የእመታ ጡዘት በህዝብ ውስጥ ለማስረጽ የሚደረገው ጥረት ከ70 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ባላት አገርና ወደ ዘጠና የሚጠጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በህጋዊነት በሚንቀሳቀሱባት ምድር ላይ መነሳቱ በርካታ ጥያቄዎችን ያጭራል፡፡ በሶስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ከተከሰተውን ምስቅልቅል ሁኔታ አንጻር ገዢው ፓርቲ የቱንም ያህል አስቀድሞ የሚዘጋጅበት የእቅድ መርሃ ግብር ቢኖረው የሃሳብ ዘውጉ አሸናፊ ሆኖ ጠ/ሚ/ሩ ማን ሊሆን እንደሚችል (እንደሚገባው) በሚሆንበት ዙሪያ እንዲያጠነጥን አያደርግም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢህአዴግ ሊቀ መንበርና የኢፌዴሪ ጠ/ሚ/ር ስልጣን የቱን ያህል እንደሰለቻቸውና በተደጋጋሚ «በቃኝ» እያስባላቸው እንዳለ መመልከቱ ለህዝብና ለአገር መሪነት

አማላይ ቃል-ኪዳኖችን በመደርደር ካልመረጣችሁን ከሚሉት ዴሞክራሲያዊ አገራት መሪዎች ጋር ስናነፃጽረው አሳሳቢ ችግር አለበት፡፡ አገርን መምራት ታላቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ለረዥም አመታት ሲዘልቅ ግን ማድከሙ (ማታከቱ) እንደማይቀር እንገነዘባለን፡፡ ደክሞኛል፣ ታክቶኛል እያሉ መምራትም የተፈለገውን ግብ እንዳይመታ ያደርጋል፡፡ የደሞክራሲ አይነተኛ መገለጫ ፍላጐቱ ያለው ራሱን ለምርጫ የሚያቀርብበት ብዙሃን ድጋፋቸውን ወይም ንፍገታቸውን በማሳየት የሚመሰርቱበት ግልጽ አስተዳደር ነው፡፡ ህዝብ በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ድምፁን የሚሰጠው ማንኛውም ፓርቲም ሆነ ግለሰብ የቱንም ያህል ረዥም አመታት በገዢ ፓርቲነት ቢቆይ ተገቢ አይደለም የሚል እሳቤ /እምነት/ የለም፡፡ የገባቸውን ቃል ኪዳኖች እየፈፀመ ነው? የሚለው ግን ያሳስበናል፡፡

ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ በሚያራምደው የግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ልማትና እድገት እንደሚያመጣ ይገልፃል፡፡ ድርቅ ርሃብና መፈናቀል ግን እንደ አመት በአል በየአመቱ ይደጋገሙብናል፡፡ የህዝቡ ቁጥር ሃያም ሰላሳም ሰባም ሚሊዮን ሆኖ ሁልጊዜ የምግብ እጥረት አለ፡፡ ዋንኛው መተዳደርያም ግብርና ነው፡፡ ወይ ፖሊሲው ወይ አፈፃፀሙ ችግር አለበት ማለት ነው፡፡ በተፈጥሮና በአፈፃፀምና በዓለም አቀፍ ተቋማት ላይ ማሳበቡ ግን የአስፈፃሚነት ሚናን ምንነት ያለመረዳት ካልሆነ ለችግሩ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ የዝናብ እጥረት ለዘመናት ሲያስቸግረን የኖረ እንጂ ትናንት የመጣ አይደለም፡፡ የመንግስትነት ሚና ዝናብ ባለበት ዘመን መወደስ፣ ዝናብ ሲጠፋ መወቀስ ሳይሆን አማራጭ ፓሊሲዎችንና አሰራሮችን በመፈተሽ ለሕዝብ የተሻለ ነገር መስራት ነው፡፡ ያን ጊዜ ዜጎች ይበጀናል የሚሉትን ያገኛሉ፡፡ ይመርጣሉ!

ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ግብአት ከሆኑት ጉዳዮች ሌላው በዘንድሮው «የዴሞክራሲ ቀን» ላይ በመሪ ቃልነት የሰፈረው የፖለቲካ መቻቻል ነው፡፡ የፖለቲካ መቻቻል የተለያዩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች የሚመሩበት ስርአትና የየራሳቸው አመለካከት ቢኖራቸውም ተከባብረው የሚጓዙበትና አላማቸውን በነፃነት የሚያራምዱበት ስርአት ነው፡፡ ሰፊ ውይይቶችና ድርድሮች ተካሂደው የሚያስማሙ ሃሳቦችና አጀንዳዎች ለፍሬ የሚበቁ ከሆነ በእርግጥም የፖለቲካ መቻቻል ሰፍኗል እንላለን፡፡ በተግባር ስናያቸው የኖርናቸው ውይይቶችና ድርድሮች ግን መጨረሻቸው መለያየትና የአቤቱታ መግለጫ የሚወጣባቸው ሆነዋል፡፡ ይህ ባህል ፈጽሞ መወገድ ይኖርበታል፡፡

በቅርቡ ገዢው ፓርቲና ተፎካካሪዎች ያደረጉት ድርድርም በቅሬታ የተቋረጠበት ተሞክሮ አለ፡፡ ድርድሩን ያቋረጡት ወገኖች በመድረኩ ላይ በተቃዋሚነት ስም አብረው የቀረቡት ከአቋማችንና አላማችን የተለዩ ስለሆኑ በተመሳሳይ አጀንዳ ልንደራደር አንችልም አሉ፡፡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተለያዩ አመለካከቶችን የሚያራምዱ ቡድኖች በአንድ ጫማ ውስጥ ይቁሙ ብሎ ማስገደድ፤ ይህ ካልሆነ አልደራደርም ማለት የዴሞክራሲያዊነት መገለጫ ሊሆን አይችልም፡፡ ኢህአዴግ ግን ይህን የቅሬታ ሃሳብ ተቀብሎ ተመጣጣኝ መድረክ ከማዘጋጀት ይልቅ «ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ነው» አለ፡፡ እኔ በመረጥኩት መስመርና አሰራር ካልሆነ በስተቀር የሚለው አመለካከት ተገቢነት የጎደለው ነው፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የፖለቲካ መቻቻላቸው ምን ይመስላል? ስንልም አሳሳቢ በሆኑ የችግር ሐረጎች እንደተተበተቡ እናያለን፡፡ ህጋዊ ሰርተፍኬት ያላቸው ሰማንያና ዘጠና ፓርቲዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ምን እያደረጉ ነው? ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች እንዲጠበቁ ከሚመለከታቸው ወገኖች

ጋር በጣምራ እየሰሩ ነው? የፖለቲካ ንቃተ ህሊና እንዲስፋፋ ሕዝቡን እየቀሰቀሱና እያደራጁ ነው? ግልጽና አማራጭ ፖሊሲዎች አሏቸው? በውስጣቸው ዴሞክራሲያዊ አሰራር አለ? እንታገልለታለን ለሚሉት ህዝብ አክብሮትና ቁርጠኛ የትግል ጽናት አላቸው? ወይስ ረጋ ሰራሽና በቀላሉ የሚፍረከረኩ ይሆናሉ? እንደ ተፎካካሪ ፓርቲ ዛሬውኑ ራሳቸውን እንዲመረምሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን። የሲቪል ማሕበራት ነፃ ሆነው ተገቢውን ሥራ ማከናወን ሲችሉ፣ የሕግ አካላት ፍትህን በጊዜው ሲሰጡ፣ የመገናኛ ብዙሃን የህዝብ አይንና ጆሮ ሆነው የተቋቋመበትን አላማ ሲያስፈጽሙና ዜጎችም በግለሰብ ደረጃ ለመብቶቻቸው ቀናኢ ሲሆኑ «የዴሞክራሲ ቀን» ተገቢውን ትርጉም ይይዛል። ያ ቀን እንደሚመጣም ተስፋ እናደርጋለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

# Verbatim

«የኛ መጣላት ኢህአዴግን የሚያስፈነጥዘው ከሆነ ይፈንጥዝ፣ከጠራን በኋላ ጥንካሬያችንን ያውቃል።»

ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም

**በእናንተና በአንድነት ስራ አስፈጻሚ መካከል የተፈጠረው አለምግባባት ኢህአዴግን ያስደስተዋልና ለምን አስፈለገ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ**

«ምንም እኮ ችግር የለውም። ቻይናዊያንን ተመልከት፣ ሂድና ሞሪታኒያ፣ኢራን ማዳጋስካርና ሆንዱራስ ያለውን ጠይቅ አውሮፓ ውስጥም ቢሆን ለፖለቲካ ቅርብ የሆኑ ዜጎች ቁጥራቸው 18 በመቶ ግፋ ቢል ደግሞ 20 በመቶ ብቻ ነው።»

አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ
የኤርትራው ፕሬዚዳንት

**ኤርትራ ነጻነቷን ካገኘችበት ጊዜ ጀምሮ ምርጫ ተደርጎ አያውቅም። ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የለም በአገሪቱ አንድ ፓርቲ(ህግዴፍ) ብቻ ነው ያለው?» ተብሎ ሰሞኑን «*ከፋይናንሲያል ታይምስ* » ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ**

«እኔ እንደማስበው ይህ ትንታኔ፣ ሪፖርቱ ለሰፈረበት ወረቀት የወጣውን ወጪ ያህል እንኳን ዋጋ የለውም»

ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ

**ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ(ICG) ሰሞኑን ያወጣውን ሪፖርት አስመልክቶ የሰጡት አስተያየት**

# ዜናዎች

## የአፋር ክልል ከፍተኛ ባለስልጣናት በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ዋሉ

- **ከ 15 በላይ ተሽከርካሪዎች እና በርካታ ዘመናዊ ቤቶች ጥቆማ ቀርቦባቸዋል**

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተማ ልማት የምህንድስና መምሪያ ኃላፊና በመምሪያው ውስጥ የሚሰሩ ሌላ ኃላፊ በሙስና ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የውስጥ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ:: ከ15 በላይ የኮንስትራክሽንና የቤት አውቶሞቢሎች ዝርዝር ለፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በጥቆማ ቀርቧል::

የፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የክልሉ የከተማ ልማት የምህንድስና መምሪያ ኃላፊ የሆኑትን አቶ አደም አብዶ እንዲሁም አቶ ጀማል አሊን አስመልክቶ የቀረበለትን ጥቆማ ሲመረምር ከቆየ በኋላ ተጠርጣሪዎቹ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ በማድረግ የፍርድ ሂደቱ ባለፈው ሳምንት በፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት የአራዳ ምድብ ችሎት መታየት መጀመሩን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል:: ተመዝብሯል የተባለው የህዝብና የመንግስት ንብረት ዝርዝር በርካታ ከመሆኑ አንፃር የክልሉ መስተዳድርና ፍትህ ቢሮ ጉዳዩን እንዴት እንዳልተመለከተው ለመጠየቅ ያደረግነው ጥረት ባይሳካም በተለያዩ ጊዜያት ጥቆማ መቅረቡን ምንጮቻችን ገልፀዋል::

የፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ጥቆማውን ካቀረቡት ወገኖች ጋር በመተባበር ተጠርጣሪዎቹን በቁጥጥር ስር ያዋለ ሲሆን ተመዘበረ ስለተባለው ንብረት ከፖሊስ ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጠን ጠይቀን ጉዳዩ በህግ የተያዘ በመሆኑ እልባት ሳያገኝ በፊት ማብራሪያ መስጠት እንደማይቻል ተገልጿል::

# ወ/ሪት ብርቱካን የቀድሞው የኢትዮጵያ ካርታ ተበረከተላቸው

**- አመራሩን የሚያስታርቅ ሌላ ዙር ሽምግልና ተጀመረ**

በአውሮፓ-ስዊድን  ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሲወያዩ በቅድመ ሁኔታ የተሰጣቸውን ይቅርታ የሚጥስ ንግግር አድርገዋል በሚል የተሰጣቸው ይቅርታ ተነስቶ  ወደማረሚያ ቤት የተመለሱት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ከምስራቅ ጉጃም ዞን የአንድነት አመራሮች የቀድሞው የኢትዮጵያ ካርታና ሰንደቅ ዓላማ ተበረከተላቸው፡፡

የምስራቅ ጉጃም ዞን የተለያዩ ወረዳዎች የአንድነት ፓርቲ አመራር የሆኑት 23  ያህል አካላት ባለፈው ሳምንት ወደ አዲስ አበባ የመጡት ሁለት አላማዎችን አንግበው እንደሆነ ከጽ/ቤቱ አካባቢ ያገኘ ነው መረጃ አመልክቷል፡፡ እንደ መረጃ ምንጮቻችን አገላለጽ የምስራቅ ጉጃሙ የአመራር ቡድን በእስር ላይ ለሚገኙት መሪው የቀድሞውን (የኤርትራ ግዛት የሚጠቃልለውን) የኢትዮጵያ ካርታ በልዩ ቅርጽ አዘጋጅቶ በወላጅ እናታቸውና በልጃቸው አማካይነት ያስረከበ ሲሆን የተልዕኮው ሁለተኛ ግብ ደግሞ በመከፋፈል ላይ ያለውን አመራር ማሸማገል ነበር፡፡

የአመራር ልዑኩ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ የሥራ አስፈጻሚ አባላትንና በቅርቡ ከፓርቲው ተሰርዘዋል የተባሉትን እነ ፕ/ር መስፍንን በተናጠል ለሰአታት ያነጋገረ ሲሆን እርቅ የሚፈጠርበትና ፓርቲው የሚጠናከርበትን አማራጭ በማቅረብ ወደክልሉ መመለሱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ለመድረክ የቀረበለት የድርድር  ቀነ ገደብ የፊታችን አርብ ያበቃል

በግንቦት ወር 2002 ዓ.ም በሚደረገው 4ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ፓርቲዎች ሊከተሏቸው በሚገቡ የስነ-ምግባር ህጎች ዙርያ ኢህአዴግ፣ መኢአድ፣ መድረክ፣ ኢዴፓና ቅንጅት ለድርድር ተቀምጠው የነበረ ሲሆን መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ ግን «ድርድሩ በተናጠል በእኛና በኢህአዴግ ብቻ ካልሆነ በጋራ መቀጠል አልችልም» በማለት ድርድሩን በመጀመሪያው ቀን ማቋረጡ ይታወሳል፡፡

ከመድረኩ መውጣት በኋላ አራቱም ፓርቲዎች (ኢህአዴግ፣ መኢአድ፣ ቅንጅት እና ኢዴፓ) ድርድሩን ቀጥለው ከስምምነት ደርሰዋል:: ሆኖም መድረክ በድርድሩ ውስጥ እንዲካተት በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደርና  የኤምባሲው የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ ባደረጉት ጥረት ተደራዳሪ ፓርቲዎች «መድረክ» ድርድሩን እንዲቀላቀል የፈቀዱ ሲሆን በስምምነቱ ላይ ፊርማቸውን ለማኖር ተስማምተዋል::

ኢህአዴግን ጨምሮ አራቱም ተደራዳሪ ፓርቲዎቹ እንዳሉት «የፖለቲካ ምህዳሩ  ጠቧል በሚባልበት በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ መድረኩ በሁኔታው ላይ መክሮ ድርድሩን እንዲቀላቀል  በማድረግ በኩል ጊዜ በመስጠት የምንችለውን እናድርግ» በማለት ካለፈው አርብ (መስከረም 8/2002) ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፊታችን አርብ ድረስ መድረኩ ድርድሩን እንዲቀላቀል የአንድ ሳምንት ጊዜ ቀነ ገደብ መስጠታቸውን ገልፀዋል::

በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አውራምባ ታይምስ ያነጋገራቸው የመኢአድ  ም/ፕሬዚዳንት ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ በሂደቱ ውስጥ የተለያዩ ስምምነቶች መኖራቸውን አስታውሰውው በዚህ አጀንዳ ላይ ግን «ዝርዝር መረጃ መስጠት የሚቻለው በድርድሩ ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች በሚሰጡት የጋራ  መግለጫ ብቻ ነው» በማለት ተጨማሪ መረጃ ከመስጠት ተቆጥበዋል::

# ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ ለጠ/ሚ መለስ ምላሽ ሰጠ

በቅርቡ የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓትን እና ያስከተለውን ውጤት አስመልክቶ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የተባለ ዓለም አቀፍ ተቋም «Ethiopia: Ethnic Federalism and its Discontents» በሚል ርዕስ የኢትዮጵያን መንግስት የሚተች ሪፖርት ማውጣቱ ይታወሳል:: ተቋሙ ባወጣው ሪፖርት በኢትዮጵያ እየጨመረ በመጣው የብሔር ውጥረቶች እና ልዩነቶች አማካኝነት ግጭት ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ጠቁሟል:: ይህንን አስመልክቶም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም በጽ/ቤታቸው ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ውይይት ተቋሙ ከኤርትራ ጋር በቅርብ እንደሚሰራ ጠቅሰው «የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ» ሲሉ ሪፖርቱን ተችተውት ነበር:: የኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የአፍሪካ ጉዳዮች ምክትል ዳይሬክተር የሆኑት ዳንኤላ ክሮስላክ ባሳለፍነው ሳምንት ለጠ/ሚ/ሩ ትችት ምላሽ መስጠታቸው ታውቋል::

ተቋሙን ከሚያንቀሳቅሰው የገንዘብ ምንጭ ጋር በማያያዝና ከዚህ ቀደም በተለያዩ ሀገራት ለምን ዓይነት ተግባሮች እንደዋለ በማስታወስ የሪፖርቱን ሚዛናዊነት የነቀፉት አቶ መለስ የአፍሪካ ቀንድን በተመለከተ የተቋሙን ሥራ የሚሰራው በአንድ ወቅት  የኤርትራ መንግስት አምባሳደር የነበረ ግለሰብ መሆኑንም ገልጸው ነበር:: ይሁንና ግን ምክትል ዳይሬክተሯ ለአሜሪካ ድምጽ ጋዜጠኛ ለትዝታ በላቸው እንደገለፁት የተቋሙ ሠራተኛ የነበረው ኤርትራዊ ግለሰብ ከዓመት በፊት ከተቋሙ

መልቀቁንና ይህንንም ሪፖርት አለማዘጋጀቱን ጠቁመው በሪፖርቱ ላይ ምንም ዓይነት የኤርትራ ተሳትፎ አለመኖሩን አስታውቀዋል፡፡

ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ እንደዚያ መፃፉ ብዙም እንዳላስገረማቸው በጋዜጣዊ መግለጫው ወቅት የተናገሩት አቶ መለስ «ከበስተጀርባ ትልቅ ባለሀብት አለ፡፡ ትርፍ ገንዘብ ያለው ትልቅ ባለሀብት፤ እናም በትርፍ ገንዘብ አማካኝነት የፖለቲካ ቁም ነገር ለመስራት የሚፈልግ፡፡ ያ ቁምነገር ግን እኛ ቁም ነገር ብለን በምንፈርጀው መልኩ አይደለም፡፡» ብለው ነበር፡፡

ምክትል ዳይሬክተር ክሮስላክ ከበስተጀርባ ተቋሙን የሚያንቀሳቅሰው የገንዘብ ምንጭን በተመለከተም ለኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉት ድርጅቶች በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ መዘርዘራቸን ገልፀዋል፡፡ በዚህም የአውስትራሊያ፣ የቤልጂም፣ የካናዳ፣ የቼክ ሪፑብሊክ፣ የዴንማርክ፣ የሆላንድ፣ የጃፓን፣ የኒውዚላንድ፣ የኖርዌይ፣ የስዊዘርላንድ፣ የቱርክ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ የእንግሊዝ እና የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መሥርያ ቤቶች ወይም የእርዳታ ድርጅቶች የተቋሙ ድጋፍ ሰጪዎች መሆናቸው ሲዘረዘር፤ አፕን ሶሳይቲን፣ ዘ ሮክ ፌለር ብራዘርስ ፈንድ፣ የኒው ዮርክ ካርኔጂ ኮርፖሬሽን፣ ዊልያም እና ፍሎራ ሂውት ፋውንዴሽንን ጨምሮ 10 ዋና ዋና የግል ተቋማት መኖራቸውም ተገልጿል፡፡

የብሔር ፌዴራሊዝም ሥርዓት ውስጣዊ የፖለቲካ ቅያሜዎችን ማስከተሉን የሚያትተው ሪፖርት በድምዳሜውም «ትክክለኛ መድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ ሀገሪቱን እና ክልሉን የሚያውክ ግጭት የመቀስቀሱን እድል በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመሩ [የብሔር] ውጥረቶቹ መባባሳቸው የማይቀር ነው፡፡» ማለቱ ይታወሳል፡፡

# ኤርትራ በዓለም ብዙ ጋዜጠኞች የታሰሩባት ቁጥር አንድ ሀገር ተባለች

የኤርትራ መንግስት በመስከረም 18/2001 (እ.አ.አ.) ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በአገሪቱ ማክተሙን ካወጀበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን ድረስ 30 ጋዜጠኞችና ሁለት የሚዲያ ሰራተኞች መታሰራቸውን ዋና መቀመጫውን ፈረንሳይ፣ ፓሪስ ያደረገው ድንበር የለሽ የጋዜጠኞች መብቶች ተሟጋች ድርጅት (Reporters Without Borders) አስታወቀ፡፡ ይህም ኤርትራ ባሰረቻቸው የጋዜጠኞች ብዛት በዓለም በአንደኝነት ደረጃ ላይ ያሰፈራት ሲሆን ይህም ከቻይናና ከኢራን ጋር ተስተካካይ አድርጓታል፡፡

«የኤርትራ የሂሊና እስረኞች የአሳሪዎቻቸው ጭካኔያዊ አያያዝ ተጠቂዎች ብቻም አይደሉም» ያለው ተሟጋች ድርጅቱ፣ «በተጨማሪና እንደውም በበለጠ፣ የአገሪቱ ዓለም አቀፍ «አጋሮች» ቸልተኝነት፣ ግልፅ ያልሆነ ፈቃድ ... ተጠቂዎችም ናቸው፡፡» ብሏል፡፡

በተለይ ከታሰሩት ጋዜጠኞች መካከል አንደኛው የኤርትራና የሲዊድን ጥምር ዜግነት ባለቤት በመሆኑ፣ የኤርትራ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ጋዜጠኞቹን እዲፈቷቸው ጫና እንዲደግባቸው በአሁኑ ወቅት የአውሮፓ ሕብረት የፕሬዝዳንትነት መቀመጫ በያዘው የሲዊድን መንግስት ላይ እንደሚተማመን ድርጅቱ ጠቅሷል። በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ እስረኞች ታስረው የሚገኙት በብረት ኮንቴይነሮችና ከምድር በታች ባሉ እስር ቤቶች እንደሆነ ድርጅቱ ዘግቦ፣ በመስከረም 2001 (እ.አ.አ.) የታሳሩ አራት ጋዜጠኞች አዳጋች የእስር ሁኔታን ሊቋቋሙ አለመቻላቸውን ገልጿል።

የሲዊድንና የኤርትራ ጥምር ዜግነት ያለው ጋዜጠኛ ዳዊት ይስሀቅ፣ በአሁኑ ወቅት የታገደችው ሳምታዊዋ «ሰቲት» መስራች የነበረ ሲሆን ለእስር የተዳረገውም በ23 መስከረም 2001 (እ.አ.አ.) ነበር። በዚህ ዓመት መጀመሪያ በአስመራ ወደሚገኘው የአየር ኃይል ሆስፒታል ለህክምና ተወስዶ እንደነበርና ሆኖም በአሁኑ ወቅት ግን ኢምባትቃላ በተሰኘ እስር ቤት እንደሚገኝ ድርጅቱ ገልጿል።

ዳዊት ይፈታ ዘንድ ዓለም አቀፍ ዘመቻ ቢደረግም፣ የኤርትራ ባለስልጣናት የጋዜጠኛውን የጤንነቱን ጉዳይ ምስጢራዊ አድርገውታል። ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ፣ ከሲዊዲናዊው ጋዜጠኛ ዶናልድ ቦስትሮም ጋር በግንቦት ወር መጨረሻ ቃለ-መጠይቅ ተደርጎላቸው ስለዳዊት ተጠይቀው በመለሱት ምላሽ ዳዊት የት ተይዞ እንደሚገኝ ግድ እንደሌላቸውና በጭራሽ ለፍርድ እንደማይቀርብና የኤርትራ መንግስት የእርሱን መፈታት አስመልክቶ እንደማይደራደር ተናግረው እንደነበር ድርጅቱ አስታውሷል።

ድርጅቱ አያይዞ፣ ባለፈው ሳምንት ውስጥ በደርዘን የሚቆጠሩ ለኢንፎርሜሽን፣ ለመከላከያ፣ ለውጭ ጉዳዮች እና ለብሔራዊ ደሕንነት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ ሲዚል ሰራተኞች የግላቸውን የኢ-ሜይል የ«ይለፍ ቁልፎች» ተገደው እንዲያሳውቁ መደረጋቸውን ዘግቧል።

# የኦሮሚያ ታራሚ ሾፌሮች አቤቱታ አቀረቡ

በአዳማ ከተማ በምስራቅ ሸዋ ዞን ማረሚያ ቤት የሚገኙ ሾፌሮች ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት አቤቱታ ማስገባታቸው ታወቀ። እነዚህ ከሙያቸው ጋር በተያያዘ በፈፀሟቸው ድርጊቶች ሳቢያ ተፈርዶባቸው በማረሚያ ቤት የሚገኙት ሾፌሮች አቤቱታቸውን ያቀረቡት በእነርሱ መታሰር ቤተሰቦቻቸው ተበትነውና የሚበሉት አጥተው «ፍትህ ሰፍኗል» እንዴት ይባላል በሚል እና በመሳሰሉት ምክንያቶች እንደሆነ ከማረሚያ ቤቱ አካባቢ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

አቤቱታውን ያቀረቡት ፍርዳቸው ከፍተኛ የሆነና ወደ 40 የሚጠጉ ታራሚ ሾፌሮች ይሁኑ እንጂ ከመኪና ግጭት እና መገልበጥ ጋር በተያያዘ ተፈርዶባቸው በማረሚያ ቤቱ የሚገኙ ሾፌሮች ቁጥራቸው እጅግ በርካታ እንደሆነ የማረሚያ ቤቱ ምንጮች ጠቁመዋል።

ሾፌሮቹ «የተፈረደብንን የእስር ቅጣት ብንጨርስ እንኳን የገንዘብ ቅጣቱን ከየት አምጥተን እንከፍላለን» ሲሉ ለምንጮቻችን ተናግረዋል። 12 ዓመት እና 13 ሺህ ብር የተፈረደበት አንድ የ27 ዓመት ወጣት ሾፌር «ቤተሰቤን የማስተዳድረው እኔ ነበርኩኝ፣ ሜዳ ለይ ተበትነዋል፤ አሁን ከዚህ ማን ይጠቀማል?» ሲል ይጠይቃል።

ታራሚ ሾፌሮቹ በአቤቱታታቸው የጠየቁት ጉዳዮቻቸው እንዲታይላቸው እና በተወሰነባቸው ፍርድ የተገኘው የፍትህ ሚዛን እንዲመረመርላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## መጣጥፎች

# በጎረምሳ ከመታቀፍ በማኅበር መታቀፍ!

አቤ ቶኪቻው

abeto2007@yaoo.com

ኢድ ሙባረክ!

ወዳጄ እንዴት ሰንብተዋል? እኔ እፍኝ ሽንብራ እየበላሁኝ ለሀገር ለወገን ከሰርቶ አደር ተቀጣሪ እስከ ተምሮ አደር ተማሪ፣ ከወጥቶ አደር ዘብ እስከ ለፍቶ አደር ገበሬ፣ ከጦም አደር ምስኪን እስከ ሸጦ አደር ነጋዴ ሰላም ውሎ ስቆ ተጫውቶ ያድር ዘንድ በፀሎት እየተጋሁኝ እገኛለሁኝ፡፡ ማን ተግቶ ማን ይቀራል?! (ኢቲቪዎች ሰላም ነው?)

በአንድ ወቅት ወጣት ነበርኩኝ፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ወጣትነትን ንቄ ጎልማሣነትን ናፍቄ እንዲሁ በመሀከል ስም አልባ የዕድሜ ደረጃ ላይ እገኛለሁኝ፡፡ (ቆይ ቆይ... ወጉ በዚህ መልኩ ከተጀመረ አይቀር ስለ ሰሞኑ አሰነባበቴ ላውጋ)

ሰሞኑን ለስራ ጉዳይ እጅግ በጣም ወጣት ከሆኑ «ልጆች» ጋር ወደ ክፍለ ሀገር ሔጄ ነበር፡፡ ወጣቶቹ ወጣት ብቻ ሳይሆኑ «አርቲስቶችም» ጭምር ናቸው፡፡ ታድያ ወጣትነታቸውም ሆነ አርቲስትነታቸው የዋዛ አይምሰላችሁ፡፡ ልክ እኛ «በድህነት አረንቋ ውስጥ ተዘፈቅን» እንደምንለው አይነት እነዚህ ወዳጆቻችንም «በወጣትነት እና በአርቲስትነት አረንቋ ውስጥ የተዘፈቁ» ናቸው፡፡ እህስ ታድያ ምን ሆነ? አሉኝ እንዴ? እናልዎ... ከእነዚህ ወጣታዊ አርቲስቶች ጋር እንደምን እንግባባ? ለካስ ቋንቋችን እንደ እድሜያችን እና እንደ እንደየ ሙያችን ይለያያልና «አሁን ተግባባን» ብለን ደህና ባቢሎናችንን ስንገነባ መልሶ ቋንቋችን ድብልቅልቅ ይልና ግንባታችን ፍርስርስ... ደግመን የጋራ ቋንቋ፣ የጋራ አቋም እናበጅና በሉ ግንባታችንን እንቀጥል ተባብለን ስንነሳ ድጋሚ ቋንቋችን ድብልቅልቅ፡፡ ይህ ጉዳይ ቢያስቸግረን ጊዜ ምን ይሻላል? እንዲህ ልንግባባ ያልቻልነው በምን ምክንያት ይሆን? ብሎ መጠየቅ፡፡ ማንን? «አርቲስቶቹን» እነርሱ ምን ብለው መለሱልን? «እኛ አርቲስቶች የራሳችን ሙድ አለን፡፡ ያ ሙድ ካልመጣ ስራ የለም፣ ያ ሙድ ካልመጣ ውይይት የለም፤ ያ ሙድ ካልመጣ መግባባት የለም፡፡» አሉን፡፡ እኛስ ምን አልን? «እባካችሁ አርቲስቶች ሙዳችሁን ቶሎ ጥሩትና ቶሎ ተወያይተን ቶሎ ተግባብተን ቶሎ ስራችንን ሰርተን ወደ ቤታችን እንመለስ?» አልናቸው፡፡

አፈር ስሆን ወዳጄ አርቲስት ስትል ምን ትዝ አለህ? ይበሉኝ፡- አንድ ቀልድ ትውስ አለኝ፡፡ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

አንድ ጊዜ «አርቲስቶቻችን» በሙሉ ተሰባስበው «በጠራራ ፀሀይ ተዘረፍን» ብለው ኡኡታቸውን ቅልጥ ባለ ሰላማዊ ሰልፍ ገልፀው አልነበረም? ምነው እንኳ ኮፒ ራይት ይከበር! ተብሎ አንዋር መስጊድ አካባቢ ያሉ ሙዚቃ ቤቶች ላይ ትልቅ ዘመቻ የተደረገ ጊዜ? እ... ያኔ አንድ ጋዜጣኛ እጅግ ሲያማርር ወደተመለከተው አንዱ አርቲስት ጠጋ ብሎ፡-

«እሺ ወንድሜ ስምህን ለአድማጮቻችን ብታስተዋውቅልን?» ይለዋል፡፡ «አርቲስቱ» በመፈክር ብዛት የተዘጋ ድምፁን እየጠራረገ ስሙን ያስተዋውቃል፡፡ «እሺ አርቲስት ጉበዜ» (ለዚህ ቀልድ ሲባል የአርቲስቱ ስም ተቀይሯል፡፡) «አርቲስት ጎበዜ እጅግ በጣም ስታማርር ሰምቼሃለሁኝ ዋናው ችግር ምንድነው ትላለህ?»

«በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ እኛ አርቲስቶች ላባችንን አንጠፍጥፈን አቅማችንን አሟጠን እኛ አርቲስቶች በስንት መከራ በስንት ፍዳ እኛ አርቲስቶች...» እያለ «ብሶቱን» ገለፀ፡፡ በየ አረፍተ ነገሩ መግቢያ ላይ «እኛ አትርቲስቶች የሚለውን መደጋገሙ ግር ያለው ጋዘጠኛ «አርቲስት ጎበዜ ለመሆኑ በይበልጥ ከህዝብ ጋር አስተዋውቆኛል የምትለው ዘፈንህ የትኛው ነው?» ብሎ ጠየቀው (ራሱም ለማወቅ ጓጉቶ) «አርቲስቱ» ሞቅ ያለ ፈገግታ እየፈገገ፤«የአርጋው በዳሶን ጉራጊኛ ዘፈን ታውቀዋለህ? እርሱ ላይ ከኋላ ሆኜ ሂኢ ሂኢ... የምለው እኔ ነኝ፡፡ ህዝብ የሚያቀኝም በእርሱ ስራዬ ነው፡፡» አለ፡፡ ጋዜጠኛው «አርቲስት ጎበዜ አመሰግናለሁኝ፡፡» ብሎ ተሰናብቶት ሲሄድ «አርቲስት» ጎበዜ በዛ ሁሉ የሰላማዊ ሰልፍ ግርግር ውስጥ የተሰወረውን ጋዜጠኛ እንደምንም ለመከተል እየሞከረ አንድ ጥያቄ ሰነዘረ፡፡ «መቼ ነው የሚተላለፈው?»

ይሔንን ሁሉ በምን ነበር ያነሳነው? «ሰሞኑን አብሬያቸው ስለሰነበትኩት በወጣትነት እና በአርቲስትነት አረንቋ ስለተዘፈቁት» ልጆች አወጋለሁ ብዬ ነው፡፡ እነርሱንስ በምን አነሳዋቸው? ስለራሴ የዕድሜ ደረጃ መግለጫ ስሰጥ ትዝ ብሎኝ፡፡ የእኔን ዕድሜ መግለጫ ለምን አስፈለገ? ይቀጥላል፡-

እንደ እኔ ከወጣትነት በላይ ከጎልማሳነት በታች ያሉ በርካታ ወዳጆቻችን በስም አልባ የእድሜ ክልል ከመኖር ይሻላል ብለው ነው መሰል አብዛኞቹ በወጣት ማኅበር ታቅፈው የጉልምስና ጊዜያቸውን ሲጠባበቁ አንዳንዶቹ ደግሞ የመታቀፍ ሱስ ያለባቸው ይመስል የጎልማሳነት ጊዜያቸውን ሁሉ በወጣት ማኅበር ታቅፈው (ለእንዲህ አይነቶቹ ታቅፈው ከሚለው ቃል ውስጥ «ቅ» ን አጥብቀን ልናነብላቸው ይገባል) የሞቀ ኑሮ እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ (እንደዚህ ነውንጂ በየሰበባ ሰበቡ አየተቃቀፉ የሞቀ ኑሮን ማጣጣም፡፡)

ለማንኛውም እንደ እኔ በወጣትነት እና በጉልምስና መሃከል የሚገኝ ሰው የኑሮ ውጣ ውረድ ካልያዘው በስተቀር ስለ ተቃራኒ ፆታ ጨዋታ ተጫውቶ ይጠግባል ማለት ዘበት ነው፡፡ (በቅንፍ የሚከተለውን እጠረጥራለሁኝ፡፡ ነብስ ካወቁ ሰዎች ውስጥ የተቃራኒ ፓርቲን እንጂ የተቃራኒ ፆታ ጨዋታን በቃኝ የሚል ይገኛል ለማለት አልደፍርም፡፡) (በሌላ ቅንፍ ክቡራን እና ክቡራት ተቃራኒ ፆታን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተቃራኒዎቻችንንም በመቅረብ ልዩነታችንን አቻችለን አንዳችን የሌላችንን ጎዶሎ እየሞላን ደስታችንን እናጣጥም ዘንድ እኔ ወገኛው እመክራለሁኝ፡፡) ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ዛሬ መጠነኛ ፆታ ተኮር ወግ እናወጋ ዘንድ አሰብኩኝ፡፡ (እስከ መቼ ጭምት ሆነን?) እናም ስለ ሴቶች እናወራለን፡፡

ታድያ ስለ ሴቶች ስናወራ ስለ የትኞቹ ሴቶች እናውራ? የሚለው አንገብጋቢ እና ፈታኝ ጥያቄ ሆኖ ከፊት ለፊታችን ድቅን ይላል፡፡
ረዥም ቀሚስ ለብሳ ነጠላዋን ተከናንባ እርምጃዋ እንደ ንስሃ ዝማሬ ረጋ ስላለው የሀይማኖት ሴት እናውራ...? ወይስ
«በቦሌው ጎዳና ሽር በምንልበት» ፀጉሯን የፆም የፍስግ አማርጣ ፍርፍር ተሰርታ ፊቷን ፀሀይ እንዳይጎዳው ፓውደሯን በስሱ ተቀብታ የከንፈር ቀለሟን ከአይን ቅንድብ ቀለሟ ጋር «ማች» አድርጋ (ባለ ኮስሞቲክስ ወዳጆቼ ሌላ የቀረኝን መዋብያ በመሙላት ተባበሩኝ ውለታ ከፋይ ነኝ) «ቦዲዋን» የሚያጉላ «ቦዲ» (ቦዲ ማለት የልጅነት ካናቴራ ሆኖ ሴቶቻችን ካደጉ በኋላ የሚለብሱት የልብስ አይነት ነው) ቦዲዋን ከአዲሱ ሱሪ ጋር ስለተዛመደው፤ አንደበቷ ብቻ ሳይሆን የጫማዋ ቋቋታ ሁሉ ስለሚሞላቀቀው ሴት እናውራ? እያልኩኝ በማስብበት ጊዜ ለዚህ ልማታዊ ለሆነው አምዳችን የምትስማማን ሴት ከወደ ቀበሌ ተገኘች፡፡
ይህች ሴት ከሁሉም በተለየች ልማታዊ ሴት ነች፡፡ ሲያንስ የኮንቴይነር (አርከበ ሱቅ) ተረክባ አነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ላይ ተሳታፊ የሆነች፡፡ (በነገራችን ላይ ይቺ አነስተኛና ጥቃቅን ንግድ የምትባል ነገር ግን እውነት ንግዷ ናት አነስተኛና ጥቃቅን ወይስ እኛ ደንበኞቹ ነን አነስተኛና ጥቃቅኖቹ??? ጥያቄ ምልክቱን ይጨምሩልኝ) ለማንኛውም አነሰ ቢባል አነስተኛና ጥቃቅን ከፍ ሲል ደግሞ ከፍተኛ እና ግዙፋ ግዙፍ የንግድ ስራ ላይ ተሳትፋ ምርጫ ሲመጣ ከተቃዋሚዎች ጋር በመወዳደር፣ ምርጫ ሲያልፍ ከደንበኞቿ ጋር በመደራደር ጊዜዋን ስለምታሳልፈው ልማታዊ ሴት ማውራት «በርቺ» ከሚለው የሬዲዮ ፕሮግራም እኩል ልማታዊቷን ከማበርታቱም በላይ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ የሚኖረው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም፡፡ በሚል ሃሳብ ስለ እርሷ ማውጋታችንን እንቀጥላለን፡፡
በለጥሻቸው ስሟ ነው (ለዚህ ፅሁፍ ሲባል ስሟ አልተቀየረም፡፡) ይቺ ሴት ውበቷ ድርጅቷ ሀብቷ ማኅበሯ ነውና ሌሎች የአካባቢው ሴቶች ከወንዶች ጋር ተቃቅፈው ሲሄዱ ካየች «በጎረምሳ ከመታቀፍ በማኃበር መታቀፍ...» እያለች ዜማዊ አሽሙር ጣል ታደርጋለች፡፡
ልጂት ዋዛ አይደለችም እያንዳንዱ ንግግሯ ልማታዊ ነው፡፡ እንኳንስ አደባባይ ይቅርና እቤቷ ከሰራተኛ ዋ ጋር የምትለዋወጣቸው ቃላቶች የተጠኑ እና ከስብሰባዎች ላይ የተቀዱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በቤት ውስጥ ሰራተኛዋ ያበሳጨቻት እንደሆነ «የቤቱን ህግ እና ደንብ አክብረሽ የምትሰሪ ከሆነ ጥሩ... ቀዩን መስመር አልፋለው ካልሽ ግን ቀይ ካርድ ለማሳየት እገደዳለሁኝ፡፡» ትላታለች፡፡ በለጥሻቸው «በጎረምሳ ከመታቀፍ በማኅበር መታቀፍ» በሚለው አቋሟ በርካቶች ያውቋታል፡፡ እናም ብቸኛ ነች፡፡ ይህቺን ብልህ ሴት ማን ያገኛታል? ያሉ የአካባቢው አድናቂዎቿ ለፍቅር በጠየቋት ወቅት ያወጣቻቸው መስፈርቶች ቁመተ ሎጋ ፀባየ ሸጋ ንግግር አዋቂ የተጣላ አስታራቂ... አይነት አይደሉም፡፡ የመጀመሪያው መስፈርቷ የኪራይ ሰብሳቢነት ባህሪ የሌለው ልማታዊ ወንድ ይማርከኛል፡፡ የሚል ነው፡፡ በለጥሻቸው እንዲህም ሆኖ ግን ድርጅቴ ካልፈቀደልኝ ለፍቅር ዝግጁ አይደለሁኝም ትላለች፡፡ እርሷ ለድርጅቷ ገና አንዲት ፍሬ ልጅ ናታ! ይህንን የሰሙ በርካታ የጎበዝ አለቆችና ልማታዊ ወንዶች ምነው ድርጅቷ ፈቅዶ ይቺን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መንፈስ ያደረባት ሴት ከማኃበሯ ጋር በመሆን ባቀፍኳት ብለው ሲመኙ ከርመዋል፡፡

በለጥሻቸውን እኔም እመኛታለሁኝ፡፡ ምክንያቱም እርሷ አባል ናት፡፡ እኔም ልማታዊ ግለሰብ ነኝ፡፡ ስለዚህ ለአንድ ልማታዊ ግለሰብ የአባል ባል ሆኖ ከመኖር የበለጠ የሚያስደስተው ነገር ይኖራል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡ ከበለጥሻቸው ጋር ተጋብቶ መኖር ማለት በቢፒአር እድገት የማግኘት ያኽል የሚስደስት ነው፡፡ በለጥሻቸው እስከዛሬ ባል አልሻም ብላ አባል በመሆኗ የተነሳ የበርካታ ጥቅማጥቅሞች ባለቤት ሆናለች፡፡ የመንግስት ስራ የሚበዛባት ምርጫ ሲመጣ ብቻ መሆኑን አብጠርጥሬ አውቃለሁኝ ያም ማለት በአምስት አመት ውስጥ አንድ የምርጫ አመት ስራ ሌላውን አራት አመት ደሞዝ እና እረፍት ናት ማለት ነው፡፡ ታድያ ይቺን ሴት ብመኝ ምን ይደንቃል? ይህንን ምኞቴን የሰሙ አንዳንዶች አባል ሆነህ ያላለፈልህ ብኩን... ባል ሆነህ ያልፍልህ ይሆን? ሲሉ አሽሟጠውኛል፡፡ ያሽሟጡ እኔ የመረጥኩትን መርጫለሁኝ፡፡

ወዳጄ ስጋ ለበሰ ሰው ደካማ ነውና ዛሬ በተቃራኒ ፆታ ምርጫዬ አድክሜዎታለሁኝ፡፡ ተይዤ ነውና አይፍረዱብኝ፡፡ እስቲ ወደ መጨረሻችን እናምራ፡-

<u>በመጨረሻም፡-</u>

ባለፈው ሳምንትም በመጨረሻም ላይ ያወራነው ስለ ስፖርት ነበር፡፡ ዛሬም ስለ ስፖርት እንደሚከተለው እናወራለን፡፡

ኃይሌ ገርመኝናል እውነትም ይቻላል! አሁንም ትችላለህ፡፡ «በእውነት ያለውን የሚያደርግ ሰው እርሱን አየን!» እያለ ዛገሪው እያወራ ነውና ኩራ እንደ አባ ቢላው ልጅ!! (በቅንፍ አንዳንዶች ምናለ የምርጫ ተወዳዳሪዎቻችን እንደ ኃይሌ በቃላቸው በተገኙ? ሲሉ ተደምጧል እናንት ምሬት ትጥቁ ወቀሳ ስንቁ የሆናችሁ ሰዎች ወዮላችሁ!) እኔ የምለው ከዚሁ ከስፖርት ጋር በተያያዘ የቲቪ ስፖርት ዘጋቢዋ ሂሩት ገብረአምላክ «በርሊን ለዘገባ እንደሄደች በዛው ስለጠፋች ያለችበትን ያያችሁ ወይም የምታውቁ አፋልጉን!» የሚል ማስታወቂያ ኢቲቪ ደጃፍ ተለጥፏል አሉ፡፡ አረ ጎበዝ ቀስ ቀስ እያልን አለቅን እኮ እንዴት ነው ነገሩ? መቻቻል የሚባል ነገር ጠፋሳ? ማነሽ ጋዜጠኛዋ... ምን ጎደለሽ እና ነው በዛው እልም ያልሽው? ዘግቢ ብለን ላክንሽ እንጂ አወዛግቢን ብለንሻል እንዴ? እኛ ህዳሴውን እናብስር የእናንተን መኮብለል... (በሳቅ መሞት¡)

ወዳጄ አሁን ማህከል ላይ ያለችውን ልንጫናት ነው፡፡ ሹፌሮች ተግባብተናል፡፡ ተሳፋሪዎች የመሃሏ ፍሬን ናት ተጭነናል ሲጢጢጢ! እራሳችንን ከኪራይ ሰብሳቢነትና ከትራፊክ አደጋ እንጠብቅ፡፡

አማን ያሰንብተን!

# ለአህጉር አፍሪካ ከመከራከር፤ ቆቃ ኃይቅን የመታደግ ቤት ሥራ ይቅደም!

በአለማየሁ ገ/ማርያም (ፕ/ር)

ባለፈው ሳምንት፣አቶ መለስ ዜናዊ፣ የዓለም ሙቀትንና የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከቱ ጉዳዮች አፍሪካ በስሜት አልባ ምዕራብያውያን ኢምፔሪያሊስቶች ኢ-ፍትሀዊና አሳፋሪ ጉዳት ደርሶበታል ባሉት ላይ በጣም በቁጣ ተናግረው ነበር፡፡ እጅግ ተቆጥተው፣ በሞራል ብስጭት ተሞልተው፣ በታህሳስ በኮፐንሀገን በሚካሄደው የከባቢ አየር ለውጥ ስብሰባ ላይ መላ አፍሪካ በምዕራቡ ላይ እንደማህተማ ጋንዲ አድማ ይመታል ብለው ዝተዋል፡፡ እንዲህም አሉ፡-

አስፈላጊ ከሆነ፣ አህጉሪቷን ለሌላ መደፈር ከሚያጋልጥ ከማንኛውም ድርድር ረግጠን ለመውጣት ዝግጁ ነን፡፡ አላማዎቻችንን ለማሳካት ከማንም ጋር ስንነጋገር ማንኛውንም የኃያላኖቹን ስምምነት እንዲሁ ለመቀበል አልተዘጋጀንም፡፡ . . . ከያዝነው ዝቅተኛ አቋሞች የማይጣጣም የትኛውንም ስምምነት ላለመቀበል ብዛታችንን እንጠቀማለን፡፡ . . . በጠቅላላ የአፍሪካ ሕብረት አባል አገራትን በመወከል የመደራደር ሥልጣን ያለው አንድ ቡድን አፍሪካ ትልካለች፡፡ ለእኔ ቁልፉ ነገር አፍሪካ በዓለም ሙቀት ለደረሰበት ጉዳት መካሷ ነው፡፡ ከዚ ተቋማት ያን (ጉዳት) በቁጥር በመተመን ሞክረዋል እና የተለያዩ ውጤቶችን አስቀምጠዋል፡፡ በርካታ ተቋማት ያን በቁጥር ለማስቀመጥ ሞክረዋልና የተለያዩ ውጤቶቻቸውንም አስቀምጠዋል፡፡ የገመቱት አማካዩ የገንዘብ መጠን የሚሆነው በዓመት 40 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር መካከል ነው፡፡

የአፍሪካ ሕብረት ሊቀመንበር ጂን ፒንግ (በቅርብ ሕይወታቸው ያለፈውና ጋቦንን ለ42 ዓመታት በአምባገነንነት የገዙት የኦማር ቦንጐ የረዥም ዓመታት የቅርብ አማካሪያቸው የነበሩ) የሰነዘሩት እንደውም ከአቶ መለስ ጽንፍ የያዘ ነው፡-

እንደዛ ያለው የገንዘብ ኃብቶች መምጣት ያለባቸው ከሕዝብ ድጎማ ነው መሆን አለበት የሚለው የምጠብቀው ነው፤ እናም፣ ከተለመደው የልማት ድጎማ ተጨማሪ መሆን አለበት፡፡ . . . ልንቀበል ያልተዘጋጀንበት መቀረፍ ከማይችል ከዝቅተኛ ደረጃ በላይ ከሆነ የዓለም ሙቀት ጋር ነው፡፡ . . . በመሆኑም ቃል የሚገባልን የካሳና የድጋፍ መጠን የፈለገ ቢሆን እንኳ ዝቅተኛ የዓለም ሙቀት ደረጃን የማያስጠብቅ ማንኛውንም ዓለም አቀፍ ስምምነት በጭራሽ አንቀበልም፡፡

በአፍሪካ መሪዎች «ሀሊና» ድብቅ የሞራል መነቃቃትን የሚያንጸባርቁ ቃላትንና ሀረጎችን መስማት እውነት የሚያስደስት ነው፡፡ እንደ «እንዲሁ ለመቀበል አልተዘጋጀንም»፣ «ሌላ መደፈር»፣ «ረግጠን ለመውጣት ዝግጁ ነን» ያሉ ቃላትንና ሀረጎችን መጠቀም «ተስፋ ከሰው ልጅ ጡት ለዘላለም ይመነጫል» የሚለውን አገላለጽ ሌላ አዲስ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ማህታማ ጋንዲ አፍሪካን ለዘመናት በበዘበዙ ምዕራባውያን ላይ እንዲያ ባለው ቆራጥ የሞራል ቁጣ በበለጠ ሊኮሩ አይችሉም፡፡

እርግጥ ነው ጋንዲ እንዳስተማሩ፣ «ከሰይጣን ጋር አለመተባበር ከበጎ ምግባር ከመተባበር ግዴታ አቻ ነው፡፡» በመሆኑም ፍትሀዊ ጨዋታ፣ ርትዕና ከባቢያዊ ፍትህን በተመለከተ ከሸረኞች ምዕራብያውያን የበላይ ጌቶች ጋር በጭራሽ አትተባበር! ከኮፐንሀገን የከባቢ አየር ለውጥ ውይይት

«ረግጦ መውጣት»ና «ሕጋዊነት መንፈግ» መገለጫው ያ ነው:: ማህተማ ጋዲ እንግሊዛውያን በደቡብ አፍሪካና በሕንድ የተከተሉትን ሰይጣናዊ መንገዶች እንዲተዉ ለማድረግ ብቸኛው መንገድ ካለማቋረጥ በጽናት ቅኝ አገዛዛቸውን በሕዝባዊ እምቢተኝነት፣ በተለይም በአለመተባበር ዘመቻ መፋለም ነው የሚል ክርክር ነበራቸው:: የሕንድ ሰራተኞች፣ ፖሊሶች፣ ወታደሮችና ሲቪል ሰራተኞች እንዲያድሙ ያበረታቱአቸው ነበር:: የሕዝብ የትራንስፖርት መገልገያዎችንና በእንግሊዝ የተመረቱ ምርቶችን እንዳይጠቀሙ ጥሪ አቅርበው ነበር:: በእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች አለቃዎች በተፈጸሙ በርካታ ወንጀሎችና አለአግባብ አያያዞች ላይ ተቃውሞ ለመግለጽ «ሳትያግራሃ»ን (ለእውነት፣ በጽናት መቆም) የሞራል ጦር መሳሪያ አድርገው በጥቅም ላይ አውለዋል::

ጋንዲ፣ ጥፋት አጥፊውን ለመለወጥ፣ የፍትህ ስሜት እንዲያድርበትና እንዲሁም በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥፋት ከተፈፀመበት ጋር ትብብር ከሌለ፣ ጥፋት አጥፊው በእርሱ ላይ የታቀደውን ጥፋት ሊያደርገው አይቻለውም የሚለውን ለማሳየት «ሳትያግራሃ»ን መጠቀም ዓላማቸው ነበር::

በሚያስገርምና አድናቆት በሚገባው መልኩ፣ የአቶ መለስ የመራል ቁጣ አመክንዬ ያ ነው:: ምዕራብያውያንን የከባቢ አየር ለውጥን በተመለከተ ለእውነት በማጋለጥና የሞራል ውግዘት እንዲደርስባቸው በማድረግ ከሰይጣናዊ መንገዳቸው እንዲመለሱ ለማሳመን ይቻል ይሆናል:: እርግጥ በቆራጥ የአለመተባበር እርምጃ ምዕራቡ ለፈጸመው ግድየለሽ የተፈጥሮ ብዝበዛ ተጠያቂ እንዲሆንና እንዲሁም ለአፍሪካውያን የገንዘብ ካሳ በመክፈል ማካካስም ይቻላል:: ግና የአቶ መለስ በሞራል ቁጣ መገንፈል ታአማኒ ነው? በቅን ልቦና የተባለ ነው?

ሼክስፒር፣ «ሰይጣን ለአላማው ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ሊጠቅስ ይችላል:: ቅዱስ ምስክርነት የሚያመነጭ ርኩስ መንፈስ፣ ፈገግታ ከተላበሰ ባለጋራ ተመሳሳይ ነው::» ብሎ ጽፎአል:: ኢኮኖሚስት መጽሄት በቅረቡ ባወጣው ጽሁፍ የአፍሪካ «መሪዎች» ቁጣ ግብ ሌላ እንደሆነ ቅልብጭ አድርጎ አስፍሯል፤ የበለፀገው ዓለም ለሙቀት መጨመር የተጠያቂነት ስሜት እንዲያድርበት ማድረግ ነው:: አቶ መለስ ለአህጉሪቷ ከሚሰጠው እርዳታ በእጅጉ የተነጠለ «የደም ገንዘብ» ወይም «የካርቦን ገንዘብ» እንደሚፈልጉ ግልጽ አድርገዋል:: ገንዘቡ ወደ ፊት የማይለቀቅ ከሆነ፣ የአፍሪካ ሕብረት ወደ ፍርድ ቤት ይዞት ሊሄድ የሚችል ጉደይ እንደሆነና ፍ/ቤቱንም በአጠቃላይ ለከባቢ አየር ለውጥ ተጠያቂውን እንዲዳኝለት ይጠይቃል:: አንዳንዴ በሚሳካለት የአፍሪካውያን አንድነት በቅረቡ በተካሄደ የመሪዎች ስብሰባ አሜሪካ፣ የአውሮፓ ሕብረት፣ ጃፓንና ሌሎች ክፍያው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም ለአህጉሪቱ በዓመት የተጣራ 67 ቢሊዬን ዶላር ለመክፈል ወስነው ነበር::

ጠቅላላው የከባቢ አየር ለውጥ ጉዳይ ዓላማቸው የነበረው የአፍሪካ አመራሮች ኪሶቻቸውን እንዲሞሉ በየዓመቱ የ67 ቢሊዬን ዶላር እንዲዝቁ ለማድረግ ነበር:: ለአፍሪካን የከባቢ አየር ለውጥ መፍትሄ ከመስጠት ጋር ፍፁም አንዳች ግንኙነት የለውም::

እስኪ ተጨባጩን እውነታ እንጋፈጠው:- ኢትዮጵያ የሥነ-ሕይወት አደጋ ተጋርጦባታል! ምንጩም ሰው ሰራሽ ነው:: ኢትዮጵያ በደን መጨፍጨፍ፣ በአፈር መሸርሸር፣ በሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ በበረሃ መስፋፋት እና በተለያዩ እጽዋቶች መጥፋትና የወንዞቿና የኃይቆቿ በኬሚካል መመረዝ የተፈጥሮ አደጋ ተጋርጦባታል:: በየዓመቱ በመቶ ሺህዎች ሄክታር የደንና የእርሻ መሬት

ይወድማል:: አንደ ኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ተቋም፣ በየዓመቱ 200 ሺህ ሄክታር ደን ኢትዮጵያ ታጣለች፤ አካሄዱ በዚህ ከቀጠለ አገሪቱ በ2020 ጠቅላላ የደን ሃብቷን ታጣለች:: ሌላ መረጃ የሚያሳየው በ1990ና በ2005 መካከል ኢትዮጵያ 14.0% የደን ሽፋኗን (2,114,000 ሄክታር) እና 3.6% የደን ሽፋኗን አጥታለች:: በደን መጨፍጨፍና በተፈጥሮ መኖሪያ መውደም ምክንያት የዱር እንስሳት ብዛት በአስደንጋጭ ፍጥነት እየቀነሰ ነው:: በመቶዎች የሚቆጠሩ የእጽዋትና የእንስሳት ዝርያዎች በቅርብ ከምድረ ገጽ የመጥፋት አደጋ ተጋርጦባቸዋል::

በጀርመን በሚገኝ የምርምር ተቋም (Environmental Radio Analytical Chemistry) ተመራማሪ ሳይንቲስት የሆኑት ዶ/ር ጌድዮን ጌታሁን እንዲያ ጽፈዋል:- እንደ ተ.መ.ድ ሪፖርት የኢትዮጵያ ደኖች እየተራቆቱ ነው: በአሁኑ ወቅት ከአጠቀላይ አገሪቱ ከ3 በመቶ በታች በዛፎች የተሸፈነ ነው:: .... በኢትዮጵያ ብዘሃ-ሕይወት በጣም በሚያሳዝን አኳኋን ነው የተያዘው:: የተፈጥሮ መኖሪያና በተጨማሪ የዕጽዋትና ተክሎችና ሌሎች ሀብቶች መውደም፣ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ዝቅ ያደርገዋል፣ የአገሪቱን ሀብት ይጉዳል እንዲሁም፣ የአገሪቱን መቀጠልና ደህንነት::

የቆቃ ኃይቅ ከባበያዊ አደጋ የኢትዮጵያን ከባቢያዊ ቅዥት ትንሹ ማሳያ ነው:: አንድ የቆቃ ኃይቅ አካባቢ ኗሪ እንደገለፀው፣ «እዚህ ዋናው ችግር ውሃ ነው:: ሰዎች ጤናቸው እየታወከ ነው:: እዚህ አካባቢ ያለው በጠቅላላ ይህን ውሃ ይጠቀማል:: ሌላ ውሃ የለም:: 17 ሺህ የሚደርስ ሕዝብ ከ10 ኪ.ሜ ርቀት በመምጣት ይህን ውሃ ይጠቀማል:: ውሃውን ብታፈላውም ይሸታል፤ ቀለሙን አይለውጥም:: ለመጠጣት አዳጋች ነው:: እዚህ አካባቢ ያሉ ሰዎች እምቅ ኃይል አላቸው:: ግን እያጣናቸው ነው፣ በተለይ ሕፃናትን:: ምንም ለማድረግ አቅሙ የለኝም:: ቢቻለኝ አደርጋለሁ፣ ግን አንዳች ላደርግ አልችልም::» ሌላ ኑዋሪ:- «ይህን ውሃ ከመጠጣት መሞት ይሻላል:: በሽታ እየጠጣን ነው:: ለአካባቢው ባለስልጣና ከብቶቻችንና ፍየሎቻችን በዚህ ውሃ እየሞቱ መሆናቸውን ነግረናቸዋል፤ ሆኖም አንድም አካል አልረዳንም:: አቤቱታ ማቅረብ ሰልችቶናል::»

የቆቃ ኃይቅ በካዬችን በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ ምንም አልተደረገም:: የተመረዘውን የኃይቁን ውሃ በመጠጣት ከፍተኛ የጤና እክሎች ያጋጠሟቸው የማህበረሰቡ ኑዋሪዎች አልተከሱም::

የእውነት ኃይል በምዕራባውያን የአፍሪካ ደፋሪዎች ላይ የሚተገበር ከሆነ፣ በኢትዮጵያም የማይተገበርበት ምንም ምክንያት የለም:: አዎ! በዓለም ተቀባይነት ያላቸው የፍትህ መመዘኛዎች (እንደሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ፣ የሕግ የበላይነት መከበር፣ ነፃ ምርጫና ነፃ ፕሬስ ወዘተ) እንዲኖሩ ኢትዮጵያዊያን ዓለም አቀፍ ሕጎች እና መመዘኛዎችን በማያከብር አገዛዝ ላይ ብዛታቸውን ተጠቅመው ሕጋዊነትን ቢነፍጉ እርምጃው ተገቢና አመክንዪአዊ ይሆናል:: ከዚህ አንጻር ለአህጉር አፍሪካ ከመከራከራችን በፊት ቆቃ ኃይቅን የመታደግ ቤት ስራ መቅደም የለበትም ትላላችሁ!?

**/አለማየሁ ገብረማሪያም፣ በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ/ሳንበርናንዲኖ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰርና ሎስ አንጀለስ በሚገኝ አንድ ተቋም የህግ ኮንሰልታንት ናቸው/**

# ገጠመኝ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት (አዳማ) መዝገብ ቤት አለማህተም

**በዘመድኩን አየለ**

ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ልክ ከአዳማ ሲወጡ፣ አልያም ከአዲስ አበባ ሲሄዱ ልክ አዳማ መዳረሻ ላይ ሦስት አስጐምገዥ ሕንፃዎች ይመለከታሉ:: የሕንፃዎቹ መገንባት ለአካባቢው «አባ ገዳ» የሚል ተጨማሪ ስያሜ ሲያሰጠው የቀድሞውን «ኪዳነምህረት» የተሰኘ ስያሜ ሲሻማው አስተውያለሁ:: በርግጥም ከሦስቱ ሕንፃዎች አንዱ «አባ ገዳ» ወይም የኦሮሚያ ክልል «ቤተ መንግስት» ነው:: የመሀከለኛው ሕንፃ ግን የሕግ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድበት ታስቦ የተገነባ ሲሆን ከዚህ ቀደም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፊንፊኔ ብቻ ይሰየም የነበረበትን ሁኔታ አስቀርቶ ችሎት መዋያ ሆኗል:: እንግዲህ እኔ ያለሁት እዚህ፣ እምሃከለኛው ሕንፃ ውስጥ ነው::

አንድ አብሯደጌ ቀጠሮ ኖሮበት ነው ባሳለፍነው ዓመት የመጨረሻ ቀናት በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት (አዳማ) የመገኘት እድሉ የደረሰኝ:: አምስት ወይም ስድስት የምንሆን ሰዎች ከሌሎች ባለጉዳዮች ተነጥለን ኮሪደር ላይ ቆመናል:: ሁላችንም በቀዳሚነት የምናንሰላስለው የመጣንበትን ጉዳይ ሳይሆን አልቀረም መሰል እንዲያው ሳንተዋወቅ፣ ሳንነጋገር ተግባብተናል:: ታዲያ ከመካከላችን የቆመች የአንዲት እናት ድምጽ ከማንሰላሰል አለፈና የአምስታችንንም ወይም የስድስታችንንም ጆሮ ተዋሰ::

«የኔስ የተለየ ነው...»፣ ሴቲቱ እየደጋገመች «የኔስ የተለየ ነው...» ትላለች:: ማነሳሻ ጥያቄ መፈለግ ስለገባኝ፣ «ምንድን ነው ጉዳዩ?» አልኩኝ:: ሌሎቹም እንደዚሁ ተያያዥ ጥያቄዎችን ጠየቁ:: ሴቲቱ እኛ መሃል ልትገኝ የቻለችበት ምክንያት ልጇ ቀጠሮ ስለነበረው ነው:: እናም እንዲያ የሚያብከነክናትን ጉዳይ አጫወተችን::

ልጅ የጉርምስና ዕድሜ ክልል ሆኖበት ከትምህርቱ ይዘናጋ ጀምሯል:: እናት ሥራ በምትውል ጊዜ የቤቱን «ዲቪዲ» ማጫወቻ እየያዘ ጓደኞቹ ቤት ፊልም ሲያይ ይውላል:: እግረመንገዱንም ጫት እና የመሳሰሉ ማዘናጊያ መሣሪያዎችን ይጠቀማል:: እናት ነገሩ እየገባት ሲመጣ ቁጣና ምክር ተጨማሪ ሥራዎቿ ሆኑ፤ አልተሳካም እንጂ:: ኋላ እንዳስቸገራት ለፖሊስ ትናገርና ልጅ እስር ቤት ይገባል:: ፖሊስ ማስረጃ አሰባስቦ ለአቃቤ ሕግ፣ አቃቤ ሕግ ደግሞ ክስ መመስረት:: ከዚያም ልጅ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሁለት ዓመት ይፈረድበታል:: ከዚያም እናት አይሆኑ ቁጭት ገባት፤ «እጄን በእጄ ...» አሰኛት:: እራሷ ተሯሩጣ ለልጇ (በስሙ) ይግባኝ ጠየቀች፤ እናም ዛሬ በቀጠሮ ቀን የልጇን ስም መጠራት እየተጠባበቀች ትብከነከናለች::

ይኼንን እየሰማን ከነበርን አምስት ወይም ስድስት ሰዎች መካከል የተወሰንነው ሴቲቱ ባጫወተችን ታሪክ ውስጥ (ምናልባት የአንድ ወገን ስለሆነ መሰል) አንዳች ክፍተት ተመልክተን ስለነበር «ሌላ ወንጀል ፈጽሞ እንደው?» ስንል አከታትለን ጠየቅን - ሁለት ዓመት መባሉ አስደንግጦን:: ሴቲቱ ግን እራሷን ወደ ጐን ነቀነቀችው:: ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ያሳለፈውን ውሳኔ

የጽሁፌ ማሳመሪያ ይሆን ዘንድ ወደኋላ ላቆየውና እኔ ራሴ አሁን ባለንበት ሕንፃ ውስጥ የገጠመኝን ላጫውታችሁ::

በዚያኑ ሰሞን ነው፤ ግን ልክ በ2001 የመጨረሻ ቀን:: የአብሯደጌን የፋይል ግልባጭ ለመውሰድ የያዝኩትን ማመልከቻ አስመርቼ መዝገብ ቤት ደርሻለሁ:: ሆኖም ገና ከመግባቴ (የመዝገብ ቤቱ ኃላፊ ሳይሆን አይቀርም) «ዛሬ ወደክፍለ ሀገር የሚሄዱ ፋይሎችን በመረካከብ ላይ ስለሆንን ማንንም እንዳታስተናግድ» በማለት ለሌላው የመዝገብ ቤት ሰራተኛ ትዕዛዝ አስተላለፈለት:: ልምምጥ ዋጋ ቢኖረው ብዬ «እባክህ፣ የኔ ጉዳይ ጊዜ አይፈጅም፤ ኮፒ አድርጎ መስጠት ነው:: ግልባጭ ነው የምፈልገው::» በማለት የያዝኩትን ማመልከቻ አሳየሁት:: ነገር ግን ልምምጤ ዋጋ አጥቶ፣ የዚያን ቀን ምንም ዓይነት ባለጉዳይ እንደማይስተናገድና በሚቀጥለው ሣምንት ወይም በ2002 ዓ.ም እንድመለስ ተነገረኝ:: መመለስ፤ ከፍርድ ቤቱ እስከ አዳማ ከተማ እንኳን ምን ያህል ሩቅ ነው?

ከሀገራችን የቢሮ አሰራር ሁኔታ አንፃር ይህንን ብዬ ባቆም ገጠመኜ «ገጠመኝ» የማይሰኝና የተለመደ ይሆን ነበር:: ደግሞ በ2002 በ«አዲሱ» ዓመት እዚያው መዝገብ ቤት፣ ያንኑ የውሳኔ ግልባጭ ለመውሰድ ተመለስኩኝ:: የመዝገብ ቤት ሰራተኛውን ነበር ያገኘሁት:: «ፎቶ ኮፒ ላነሳልህ እችላለሁ፣» ሲለኝ የእፎይታ ትንፋሽ መተንፈስ ጀምሬ ነበር:: ግን «ግን...» ሲል ሌላ ዓረፍተ ነገር ጀመረ:: «ግን ... ማህተም የለም::» አግራሞቴን ተመልክቶ ድምጽ ባላወጣም «እንዴት?» የሚል ጥያቄ አየጠየኩት መሆኔ ገባውና «ከፋይሎች ጋር ወደ ክፍለ ሀገር ሄዷል» አለኝ - ማህተሙን ነው:: መዝገብ ቤት አለማህተም!

ባለፈው ዓመት መጥቼ መዝገብ ቤቱ በፋይል ርክክብ ሥራ እንደበዛበትና በሚቀጥለው ዓመት ና እንደተባልኩኝ ለመዝገብ ቤት ሰራተኛው አስታወስኩት፤ አስታወሰኝ:: አስከትሎም ማህተሙ መዝገብ ቤቱን ጥሎ የጠፋው ያኔ እኔ ማመልከቻ ይዤ በመጣሁበት ቀንና ዛሬ አናስተናግድህም በሚጠቅለው ሣምንት ና ከተባልኩበት ሰዓት በኋላ መሆኑን ነገረኝ:: እንደገና አስከትሎም ማህተሙ ከ15 ቀናት በኋላ ሊመለስ እንደሚችል ማስተሳዘኛ ቢጤ መረጃ አቀረበልኝ::

መቼም «ሥራ በዝቶብናል» ሲሉኝ ሥራ ፈትተው አይደለምና ይሁን፤ ነገር ግን ማህተም እንደማይኖር እያወቁ፣ አለማህተም እንደማልስተናገድ እያወቁ በሌላ ቀን መቅጠር ምን ይባላል:: «እያወቁ» ብሎ መደምደም ላይቻል ይችላል፤ መዝገብ ቤቱ ግን አለማህተም ለሥራ ክፍት መሆኑ ግር ያሰኛል:: አለማህተም ምን ዓይነት ሥራ ሊሰራ ይችላል? ማህተሙንስ ወደ ክፍለ ሀገር ከመውሰድ ሌላ ማህተም ማዘጋጀቱ ከተጠናወተን ባለጉዳይን የማንገላታት ደዌ የምንላቀቅበት ፍቱን መዳኒት ሊሆን አይችልም ነበር? ይህ አሰራር ተጠያቂነትን ለማጽናት ተብሎ የተዘረጋ ከሆነ ደግሞ በሀገሩ ማህተሙን ይዞ ከሚንቀሳቀሰው ግለሰብ ውጪ የተጠያቂነት ኃላፊነትን መሸከም የሚችል ተጨማሪ ሰው ይጠፋልን?

በነገሬ ላይ፣ መዝገብ ቤቱ ከ2001 ወደ 2002 የተሸጋገረው አለማህተም ነው:: እናም ያገር ሰው «መልካም አዲስ ዓመት» ሲል የሚመኘው አለምክንያት አይደለም:: ያገር ሰው «መልካም ዓመት» ብቻ ሳይሆን «መልካም አዲስ ዓመት» ነው ያለው:: እንደገባኝ ከሆነ የያዝነው ዓመት ካለፈው ካልተለየ፣

አዲስ ካልሆነ መልካም አይደለም:: ዓመቱን አዲስ የሚያደርገው የእኛ ሁኔታ መለወጥ እንጂ የፀሃይዋ አወጣጥ ስላለመሆኑ የሚጠራጠር ካለ እርሱ ለውጥ ያስፈልገዋል::

ከሁሉም ከሁሉም እጅግ የሰቀጠጠኝን ልንገራችሁ:- የመዝገብ ቤት ሰራተኛው ማህተሙ ከ15 ቀን በኋላ እንደሚመለስ ሲነግረኝ ግልባጭ ፋይሉ የተፈለገው ይግባኝ ለመጠየቅ እነደሆነና ጊዜ እንዳይነጉድ መስጋቴን አስገነዘብኩት:: እርሱ ግን «ችግር የለውም 90 ቀን አለህ::» አለኝ - በማህተም ችግር አብሯደኔ ምክንያት የለሽ 15 ቀናትን በእስር ሊያሳልፍ መሆኑ አላስጨነቀውም ወይም አልመጣለትም:: በርግጥ የመዝገብ ቤት ሰራተኛው በኔ መንገላታት ማዘኑን ገልጾ ይቅርታ ቢጠይቀኝም አላረካኝም፤ ይባስ ከነከነኝ:: አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም እስከመቼ ሦስት እና አራት ጊዜ እንመላለሳለን፤ ለዚያውም ሀገር አቋርጠን:: ይህ ችግር በኦሮሚያ ብቻ እንዳልሆነ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ነኝ፤ እኔ ብቻ ሳልሆን ክልላዊ መንግስታቱም፣ የፌዴራል መንግስቱም እርግጠኛ እንደሆኑ እርግጠኛ ነኝ:: ኀበዝ የያዝነውን ዓመት ካለፈው የተለየ እናድርገው፤ የባለጉዳይ (የህዝብ) ተቀጣሪዎች መሆናችንን አንዘንጋ! ሌላው ቢቀር በመዝገብ ቤቶቻችን ውስጥ ማህተም አይጥፋ::

አሁን ደግሞ ለጽሁፌ ማጣፈጫ ብዬ የቆጠብኩትን የሴትይቱን ነገር ልጨርስላችሁ:: የልጇ ስም ከችሎቱ ሲጠራ በፖሊስ ታጅቦ የሚገባውን ልጇን ተከትላ ከችሎት ፊት ቀረበች:: ለይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለዚህ ሁሉ ምክንያት እርሷ መሆኗን የተናገረችው እናት፣ ልጇ እንዲስተካከልላት እንጂ ትምርቱን አቋርጦና ተጨማሪ ጥፋቶችን ከእስር ቤት ተምሮ እንዲወጣ ተመኝታ እንደማታውቅ እያለቀሰች መናገሯን በአካባቢው የነበሩ ሰዎች እና በኋላ ለይ ደግሞ እርሷም ገልጸውልናል::

ፍርድ ቤቱ ምን አለ? ሁለት ዓመቱ ወደ አንድ ዓመት ተቀነሰለት (ወይም ተቀነሰላት - ለእናቱ)፤ አምስት ወር ታስሮ ስለነበርም በአመክሮ ከሦስት ወር በኋላ ሊፈታ እንደሚችል ለማወቅ ችያለሁ:: ሆኖም በማረሚያ ቤት ሀቀኛ ታራሚ ሆኖ መሰንበቱ ለአመክሮም ሆነ ከእስር በኋላ ለሚገጥመው ህይወቱ የሚበጅ መሆኑን እናት የተገነዘበች ትመስላለች::

# በጉልበትህ ሂድ!!!

**ጉልበት = ክህሎት + ችሎታ**

**(የትንቢት ድምጽ)**

**(If there is a will, there is a way!)**

**በመርዓዊ ሜጌሶ**

ሰማዩ በድንገት ናስ የሆነውን ያህል፣ ለዚህ አምድ የሚሆን ትኩስ መገለጥም በሣምንቱ ችግር ሆኖ ነበር የሰነበተው:: በመሆኑም ቆየት ካለ ቋት መመልከት ግድ ሆኖብኝ ርዕሰ ጉዳዩን ላካፍላችሁ ወደድኩ:: እንዲያውም ውስጠኛው ማንነቴ እያመላከተኝ እንዳለው ከሆነ ርዕሰ ጉዳዩ አገራዊ ትንቢት ነው:: ነቢይ በጫካ ወይም በዋሻ እንደሚገኝ በማሰብ የከተማ ነቢያትን ቸል ካላልን በቀር ድምፁ ያነቃቃችኋል ባይ ነኝ:: የነፍስና፣ የአዕምሮ ጉልበትን ያለማወቅን የዋህነት፣ እንዲሁም ሥራ ላይ

ሲውል ደግሞ የሚያመጣውን መሠረታዊ ለውጥ የሚያሳይ ሀሳብ ነውና የዛሬውን በትህትና አዳምጡት።

መስከረም ፈገግ ብሎ በመገለጡም ይመስላል ዘንድሮ እየተካሄደ ባለው የመልካም ምኞት መግለጫ ብዙ ሰዎች ብሩህ መጪ ጊዜ እየተመኙ መገኘታቸውን በተለይ ወዳጄ በላይ ታዝቧል። ከአፋቸው ምሬትና ማጉረምረም የማይለየው አንድ ደንበኛው ሳይቀሩ በአንድ ሁለት ያህል ጉዳዮች የደስታ ገጽታ እንደገለጡ ሰሞኑን አስተውሎ እየተገረመ ሲነግረኝ ነበር ታዲያ - በላይ። «ሰው በልቡ እንዳሰበ እንደዚያው ነው»ና ምኞቱ መልካም ነው። የተመኘነው ይምጣም እንላለን።

ምድያማውያን አስጨንቀዋቸውና ጨቊሽትና መቃተታቸው በመብዛቱ ነበር መልዓኩ አንድ የነፃ አውጭነት ጉልበት ወዳለው፣ ነገር ግን ይህንን ማንነቱን ወዳልተገነዘበው ነፃ አውጭውና መስፍኑ ጌዴዎን መጥቶ አንተ ጽኑና ኃያል ሰው እስራኤልን ከምድያም ነፃ የሚያወጣ ጉልበት አለህና በጉልበትህ ሂድ! የሚለውን ትዕዛዝ የሰጠው። ጌዴዎን የነፃ አውጭነት እምቅ ኃይል የነበረው ቢሆንም ከምድያማውያን በመሸሽ በወይን መጥመቂያ ውስጥ ስንዴ ሲወቃ ነበር መልዓኩ ወደሱ መጥቶ ከላይ የተጠቀሰውን «የተንቀሳቀስ አሁን» ትንቢት የተናገረው። ልብ በሉ፣ ይህ ሰው ጽኑና ኃያል ቢሆንም በጽናትና በኃይሉ ለመንቀሳቀስ ግን በውስጡ የሚያላውስ ትንቢት ሊነገረው ይገባ ነበር።

ሌላው የሚገርመው ጉዳይ ይህ ሰው ጽኑና ኃያል ቢሆንም እርሱ ግን ይህ ማንነቱን (ችሎታውን) አለማወቁም ነው። ጽኑና ኃያል ነህ!! በሚል ሲነገረው ታዲያ ጌዴዎን - ማ እኔው? ወገኔ ከምናሴ ነገድ ከሁሉ ይልቅ የተናቀ ነው፤ እኔም በአባቴ ቤት የሁሉ ታናሽ ነኝ! በማለት እስራኤልን ከምድያም እጅ አድን የሚለውን ተልዕኮ ለመቀበል ተቸግሮ ነበር። ይህ መሆኑ በእጅጉ አስገራሚ ነው። ጌዴዎን በመልዓኩ የተባለው ነገር እርሱ ስለራሱ ከሚያውቀው ፈጽሞ የተለየ ስለነበር ነው ተናጋሪው ራሱ «CV»ውን ካላሳየኝና ይህንኑም በሥራ ካላረጋገጠ የተባልኩትን ማንነትና ተልዕኮ አልቀበልም ብሎ የተናጋሪውን «credentials» ለመጠየቅ የተገደደው። ይኸውም ምን ሲል ነው:- «የምትናገረው አንተ ከሆንክ ምልክት አሳየኝ፣ ይኸውም አጎዛ በውጭ አኖራለሁ በአጎዛው ላይ ብቻ ጠል (ዝናም) ይውረድ ሌላው ምድር ደረቅ ይሁን።» ሲል ፈተነው። እንደልመናው በአጎዛው ላይ ብቻ ጠል ወርዶም አንድ ቆሬ (ወይም ገበቴ) (ወይም ሳፋ) ሙሉ ውሃ ተጨመቀ።

ጌዴዎን አሁንም አንድ ፈተና ልጨምር፣ በጠጉሩ (በአገጎዛው) ላይ ብቻ ደረቅ ይሁን በምድር ሁሉ ላይ ግን ጠል ይሁን አለ። አምላክ ምን ይሳነዋል፣ በዚሁ መሠረት አጎዛው ብቻ ደረቅ ሆኖ ምድሩ ሁሉ ራሰ። የተናጋሪውን ታማኝነትት በዚህ ዓይነት ሲያረጋግጥም ጌዴዎን ማንነቱን ተረድቶ ተልዕኮውን ያከናውን ገባ።

በዛሬ ጊዜ ኢትዮጵያም በፈጣሪ አምላክ ዓይን እንደዚሁ እየታየች ነው። ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ስለራሷ ያላት ስብከት («Profile» ብለነዋል ባፈው ሳምንት) ድሃ ነኝ፤ ድርቅ አይለቀኝም፤ ሁለት ጊዜ መብላትም አልችልም፤ ኋላ ቀር አገር ነኝ፤ ከዓለም መጨረሻ ነኝ፤ እኔ በተለይ እዚህኛው ወረዳ የተወለድኩት ማንም ከግምት አያገባኝም፤ ከሁሉ የማንስ ነኝ፤ የሚል የራስ ስዕል ያላት አገር ትመስላለች። አንዳንድ ሽልማት የሚቀበሉ ሰዓሊዎችና ደራሲዎች ጭምር ጎስቋላይቱ ኢትዮጵያ! እያሉ

ግነት (fame) የተቀበሉበት አገር ልትሆን ትችላለች:: ይኼ የገዛ ራስ ስዕል ግን በልዑሉ ዘንድ ተቀይነት አለው ወይ? ነው ቁልፉ ጥያቄ፣ እናም ልዑሉ እያለ ያለው ግን ይኼ ስዕል ተለውጧል፤ አዲሱ ስዕል ይተግበር ነው::

ፈጥኜ ወደ ትንቢቱ ልምጣና በአጭሩ ኢትዮጵያ እንደዚህ እንደላይኛው አይደለችም:: ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ በጉልበቷ (potentially) የምትሄድበት ጊዜ መገለጥ ይገባዋል:: የመሬት ልማት ጉልበት፣ የውሃ ሀብት ጉልበት፣ የማዕድን ጉልበት፤ የኢንዱስትሪ ጉልበት፤ የፍትህ ጉልበት፣ የሥነ-ጥበብ ጉልበት፣ የኪነ-ህንፃ ጉልበት ... ወዘተ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ ስላለ ይኼ ጉልበት ሥራ ላይ ውሎ ከምድያማውያን (ከችግር፣ ከኋላቀርነት...) አላቅቆ አገሪቱን ቀኝ ኋላ ዙር አሰኝቶ የሚያልፅቅ (ከፍ የሚያደርግ) ጉልበት ከብዙዎቻችን ይለቀቅ ዘንድ የሚገባበት ዘመን ነው:: ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ በጥበብ ቀሚስና በጋሻና በጎራዴ ብቻ ሳይሆን (ይኼ የድሮ ኢትዮጵያ ታሪክ ነው) ባለብዙ ህብረ-ቀለመ ያሸበረቀችና ያልታየች ኢትዮጵያ ልትሳልልን (portrayed) ይገባል:: አሁን ያለው የኢትዮጵያ ስዕል በቂ አይደለም:: አሁን ያለን ወይም ያለፈን ነገር መሳል (መጻፍንም ይጨምራል) ብቻውን በጥሪትነት አገልግሎ የቀጣይዋ ኢትዮጵያን ገጽታ በራዕይ ካላየን በአሮጌ ስዕል ብቻ መኖሩ ትርጉም የለሽና እርጅናም ነው:: እርጅና በመሠረቱ ባለፈ ታሪክ ብቻ መኖርና ለወደፊቱ ራዕይ ማጣት ስለሆነ ከዚህ በኋላ ያረጀ ያፈጀ (Archaic) አስተሳሰብ በኢትዮጵያ ስፍራ ሊኖረው አይገባም:: በነገራችን ላይ ማርጀት አለማርጀታችሁን ለመመዘን ከፈለጋችሁ በቀደሙ ክንዋኔዎችና በድሎቻችሁ መኖር አለመኖራችሁን ልትለዩ ትችላላችሁ:: የምዘናው ውጤት «ያኔ ያኔ ድሮ» የሚለውን ብቻ የሚያስገነዝባችሁ ከሆነ ባለፈ ድል እየኖራችሁ ነውና በርግጥም አርጅታችሁዋል:: በአንጻሩ ምዘናው ያለፈውንና የአሁኑንም በመነሻነት በማየት የወደፊት መቅረጽ ካስቻላችሁ ግን ገና ብርቱ ናችሁ ማለት ስለሆነ ድንቅ ሁኔታ ላይ ናችሁ::

እዚሁ ላይ ጨምሮ ማስገንዘብ የሚጠቅመው እርጅና የዕደሜ ጉደይ ሳይሆን (በዋናነትና በመሠረቱ ማለቴ ነው) እርጅና የወደፊትን ማየት መቸገር መግለጫ ነው:: ይልቁንም ወደፊትን ማየት አለመቻል ነው እርጅና:: ለዚህም ይመስላል በተለይ ነጮቹ «How is your future?» በማለት የሚጠይቁት:: ለዚህም ጥቂት ምክር ልለግስ፣ ጭልምልም ያለ ነው! ምንም አይታየኝም! ልትሉ በማይገባችሁ ጊዜ ይህን አትበሉ:: ብያንስ - ላስብበት ይገባል! ማለት ብልህነት ነውና::

በቀጣዩ ምርጫም «አዲስ ኢትዮጵያን» በራዕይ በመሰነቅ ራዕዩን የሚተረጉሙበትን ዲዛይን የማይሰሩ ፓርቲዎች ወይ አርጅተዋል ወይ አይመጥኑም ስለሚባሉ ልካችሁን የምናውቀው በራዕይና በመተርጎሚያ ዲዛይናችሁ ስለሆነ እንግዲህ ራዕያችሁንም የአፈጻጸም ስልታችሁንም አሳዩን፤ ከዚያም እንደጌዴዎን የምትናገሩኝን ትተረጉሙት እንደሆነ እፈትናችኋለሁ የሚሉ ሰዎች መኖራቸው በዚህ ወቅት (season) ሊስተዋል ይገባል::

የማንኛውም ፓርቲ የፕሮግራም ሰነድ አዲስ ኢትዮጵያን ይሰራል? የሚለውን የሚለዩ ጉልበታሞች (Mighty-intellectually) አገሩ ስላሉት ሰነዱን ሥሩ! ፈጥናችሁም ለምዘናችን አቅርቡት:: እንደነገርኳችሁ ይህ ዘመን ጉልበታሞች (ክህሎተኞች) ክህሎታቸውን ሥራ ላይ ያውሉ ዘንድ

የተፈቀደበት ዘመን ስለሆነ በራዕይና በአፈፃጸም ዙሪያ የተሰናዳው ወይም እየተሰናዳ ያለው የፓርቲ ፕሮግራም አገሩን ለመለወጥ የማያስችል ከሆነ «መ» መልሱ አልተሰጠም የሚል መልስ ሊመረጥ ሁሉ ይችላል:: የአገሪቱን ጥያቄ መልስ የሚሰጠው የፓርቲ ፕሮግራም «ሀ» ነው፣ «ለ» ነው፣ «ሐ» ነው፣ ወይንስ «መ» መልሱ አልተሰጠም ነው? የሚሉ ምርጫዎች ስላሉ ማንኛችሁም ፓርቲዎች መልስ አልሰጣችሁም እንዳንላችሁ ተግታችሁ ሰነዱን ትሰሩ ዘንድ እናሳስባለን:: ባለንበት በመርጠህ በልጽግ ዘመን የሚያበለጽገውን ፕሮግራም ሥሩና ከነ «ሲቪ»አችሁ ቅረቡ፤ እንመርጣለን:: ጉዳዩን በምሳሌ ለማስረዳት ሲሞከር፣ ለምሳሌ የኢትዮጵያን የእርሻ ሁኔታ የሚለውጥና አገሩን የሚያሳርፍ ራዕይ ቀርጸህ ራዕዩን የምትተረጉምበት ፕሮግራም ካላሳየህ በእርሻ ለውጥ አይመጣምና ፕሮግራሙ ለእርሻው ጥያቄ መልስ ስለማይሰጥ መልስ አልሰጥህም ማለት መቻል አለብን:: ማንንም ሰው (ወንድ ሆነ ሴት) ከችሎታው ለይተህ ብትመለከት አገር ይጠቅማል ተብሎ አይታሰብም:: የብቃት መመዘኛ ቀዳሚ መመዘኛ መሆኑ ሊስተዋል ይገባል::

ባጠቃላይ እንግዲህ ኢትዮጵያ በሰው ኃይል ጉልበቷ የምትነሳበት ዘመን ይሁን ብዬ እዚሁ ላይ ላቁም:: ደህና ቆዩን::

# ስለምን ነፃ አውጪዎችን እናወግዛለን፤ ሙታንን እንወቅሳለን?

**በተስፋዬ ሀቢሶ (አምባሳደር)**

ፊውዳላዊው ንጉሳዊ ሥርዓት በ1966 ዓ.ም እስከተገረሰሰበት ጊዜ ድረስ ካለእፍረት ራሳቸውን «ስዩመ እግዚአብሄር» ብለው በሾሙና አገልጋይ ተገዥዎቻቸው አድርገው ለወሰዷቸው የራሳቸው ሕዘቦች ተጠያቂ ባልነበሩ ተፈራራቂ ንጉሳዊ አገዛዞች ኢትዮጵያ ለዘመናት ተገዝታለች:: የሥርዓቱን መገርሰስ ተከትሎ፣ ርዕዮተ-ዓለማዊ ማርኪሲስት አገዛዝ ለሁለት አስርት ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ በጭቆና ገዝቷል - ከ1966 አንስቶ ሕወሓት/ኢህአዴግ መራሽ ንቅናቄ(ዎች) በግንቦት 1983 ዓ.ም አገዛዙን ሙሉ በሙሉ እስከገረሰሰበት ዓመት ድረስ:: እስከዚያ፣ ዴሞክራሲን የፖለቲካ ባህልና የመንግስት ቅርጽ እንዲሁም የሕይወት መንገድ አድርጎ የሚከተል ለዴሞክራሲ ቀረቤታ የነበረው ባህል በኢትዮጵያ አልነበረም:: እናም፣ ማህበረሰባችን በትክክል የሚተገበር፣ ዴሞክራሲን ዘላቂ፣ ከጠቅላላ ተቋማትና ዘዴዎች ጋር ሥፍራውን ለማስያዝ ወሳኝ የሚባለውን ለመትከልና ቀጣይ ለማድረግ የሚያስችል የፖለቲካ ባህል አልነበረውም::

«ዴሞክራሲያዊ መንገድ» ወይም ዴሞክራሲያዊ ሲቪክ ባህል፣ «ሕዝቦች ራሳቸውን የማስተዳደር ብቃታቸውን የሚወስኑ ፀባዮችን፣ ተግባሮችንና ተለምዶዎችን» የሚያመላክት ነው (ዲያን ራቪች):: እዚህ ጋር ቁልፍ ጥያቄ፣ አንድ የተለየ ማህበረሰብ ለዴሞክራሲያዊነት ያለው ዝንባሌ መጠን ወይም ሽምፕተር፣ «ዴሞክራሲያዊ የራስ አስተዳደር» ብሎ የሚጠራው፣ በፖለቲካ ባህል ውስጥ

አለ/የለም የሚለው ነው:: ምን ለማለት ተፈልጐ ነው፣ ዴሞክራሲያዊ ባህልና ታሪካዊ ተሞክሮዎች በሌላው ማህበረሰብ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት መመስረት፣ ዘላቂ ማድረግና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ማጎልበት አዳጋች ነው::

ሌላው ቀርቶ፣ በገዥው ግንበር ደጋፊዎችና መንግስት እና በተቃዋሚ ጎራ ባሉት መካከል እየተካሄዱ ያሉ ፖለቲካዊ ድርጅቶችና ክርክሮች - በ2002 የሚካሄደው አራተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ጫፍ ላይ እያለን - አሁን ድረስ አንዱ ለሚሰጠው አመለካከትና አስተያየት አክብሮት የሚንፀባረቅባቸው አይደሉም:: አብዛኛዎቹ አሉታዊና ጥላቻ ያረገዙ ናቸው:: ይህም የሚያመለክተው በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ በሚሳተፉ ተቀናቃኞች መካከል በበርካታ ብሔራዊ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ፍፁም አለመግባባትና መደማመጥን ያካተተ መነጋገር አለመኖሩ ነው::

በተቃዋማዊ ጎራ፣ በገዢው ግንባርና የእርሱ «አጋር የፖለቲካ ድርጅቶች» በሚባሉት መካከል አለመተማመን አለ:: ቀኝ ጉንጭህን ሲመታህ ግራ ጉንጭህን ስጥ የሚለው የ2000 ዓመታት ክርስትያናዊ አስተምህሮ ቢኖርም፣ ይህን መሰሉ ፀባይ አልፎ አልፎ ነው አጽንኦት የሚሰጠው ወይም ተቀባይነት ያለው፤ እናም፣ በሰብዓዊ ፍጡራን የሚታሰብ አይደለም፣ ክርስቲያንም ተሆነ አልሆነ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ በ«አለማዊ» ፖለቲከኞች መካከል:: «እያንዳንዱ ድርጊት ተስተካካይ ወጤት አለው» እንደሚለው ኒውተን ማህበራዊ ፀባይም በተመሳሳይ ተገለቢጦሻዊ ነው- የዘራኸውን ታጭዳለህ እንደማለት::

ጥንታዊት አቴንስን ስናጤን፣ ተፈላሳፊው ጀምስ ሀሪንግተን፣ የሆብስ ተከታይና በዘመኑ የነበረ፣ እንደ «ሕዝባዊ ክርከሮች የበለጠ አደገኛ ምንም የለም» ብሎ እንደሚያስብ ምልከታውን ሰጥቶ ነበር:: በሌሎች ላይ አሉታዊና የጥላቻ ስሜት ከጫርክ፣ ከሌላኛው ወገን ተመሳሳይ አሉታዊ እና ማብቂያ የለሽ ምላሽ መጠበቅ አለብህ፣ አንዳንዴም ድርብ ድርብርብ እና ከዛም የባሰ:: ግን ለምን? ስለምን ፖለቲካዊ ድርድሮችን፣ ሕዝባዊ ክርክሮችንና ትችቶችን ለሌላው ወገን አስተያየትና አመለካከት አክብሮት በሚሰጥ ስልጡን መንገድ ማካሄድ ያዳግተናል - ርዕዮተ ዓለማችን የፈለገ ተቃርኖአዊ ቢሆን እንኳ? ስለምን ወሳኔውን ለህዝብ አንተወውም? በትክክል ግባችን ህዝብን ለማገልገል እንጂ ለራሳችን ጥቅም ካልሆነ - የፖለቲካ ስልጣን መጨበጥ እንደመጨረሻ ግብ ካልቆጠርን፣ ስልጣን ለመቀማት ሳይሆን በቂና ጥራት ያላቸው ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለህዝባችን ለማቅረብ ከሆነ ስለምን ፖለቲካዊ ክርክሮችን፣ ድርድሮችንና ትችቶችን በሰለጠነ መንገድ በመከባበር አናካሂድም?

በልሂቃን ዙሪያ፣ በምሁራን፣ በማህበረሰባዊ ስብስቦች፣ በማምለኪያ ስፍራዎች፣ በመያዶችና በአጠቃላይ በሌሎች መካከል የሚመነጨው ተጋፍጦሻዊ ፖለቲካ ወደ ቀውስ ይመራናል:: የመጀመሪያው መዋቅራዊ ቀውስ የሚመነጨው በስህተትና ፍፁም አመኔታን በማጣት የወቅቱን አገዛዝ የተወሰኑ በአገር ውስጥ ያሉና በውጭ የሚገኙ ቡድኖች ፀረ ኢትዮጵያና አገሪቱን በብሄር በመከፋፈል የመበታተን አላማ ያለው አድርገው መወሰዳቸው ነው፤ በዚህም የገዥውን ግንባርና የመንግስትን ሕጋዊነት ትልቅ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ያኖሩታል:: በጠ/ሚ መለስ የሚመራው መንግስት በእነዚህ ቡድኖች እንደ «ዘረኛ»ና የራሱን ጎሳ ብቻ በአጠቃላይ በቁልፍ የመንግስት ስልጣኖች የሚሾም ተደርጎ ይወገዛል::

ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው አደጋ በብቃት የሚሰራ ዴሞክራሲያዊ የፓለቲካ ሥርዓት፣ መልካም አስተዳደርና ወጤታማ፣ በቂና ሥነ-ምግባራዊ አሰራር እጥረት ነው፤ ይህም በጠንካራ ሕጎችና ድንጋጌዎችና የሕግ የበላይነት አለመኖርና አለመጠበቅ በይበልጥ ተባብሰዋል። ተመራጭና ተሿሚ ባለስልጣናት ብቃታቸው የግዴታ እንዲጣራና በውጤት በመመርኮዝ ግልጽነት በተላበሰ አኳኋን እንዲሰሩ ማድረግ እንዲቻል ቋሚ ሥርዓት መፍጠር ግድ ይለናል። መሪዎቻችን አብረዋቸው ሊሰሩ የሚፈልጓቸውን ግለሰብና ማናቸውንም ሰዎች የመምረጥ መብት ሊኖራቸው ይገባል፤ ሆኖም እንዲመሩን የሚያስችላቸውን ሥርዓት ግን የመምረጥ መብት አለን። ሙስና ወንጀል መሆኑ የተገለፀበት ሕግ ኢትዮጵያ ካለ ይህ ሕግ እንደግለሰብ እኔ ላይ ሊተገበር ይገባል፤ ትግሬ ወይም አማራ ወይም ኦሮሞ ወይም ከምባታ ወዘተ ነኝ ቢባልም እንኳን የፕሬዚዳንቱን ወይም የጠቅላይ ሚኒስትሩን ወንድም ወይም ልጅ ሕጉ እንደመግዛቱ ማለት ነው።

ሕጉ ቋሚ መሆን አለበት። መንግስታት ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ። ሆኖም ሥርዓቱ ሊቆይ ይገባል። የግዴታ እዛው መኖር አለበት። ስለዚህም የጠ/ሚ መለስ ዜናዊ አመራር በፍትሐዊ፣ ነፃና ተቀባይነት ባለው ምርጫ ወደ ስልጣን ይመጣል፣ በፌዴራል ደረጃ በርካታ ስልጣኖች በሕወሓት/ኢሕአዴግ ካድሬዎች ወይም ደጋፊዎች ይያዛሉ። ሆኖም ሙስና ወንጀል ነው ብሎ በሚደነግግ ሕግ ይገዛሉ። እናም፣ በሙስና የተያዘ ማንኛወም ለመቀጫ ይህ ሕግ ይተገበርበታል። ሕጉ አንድ አይነት እንደሆነ ይዘልቃል። ሁሉም ሰዎች በሕግ እኩል ናቸውና።

ቋማና ግልጽነት የተላበሱ የሲቪል ሰርቪስና ከአድሎአዊነት የተላቀቀ፣ ገለልተኛና ተዓማኒ የምርጫ ሥርዓት መፍጠር ይጠበቅብናል። እንደኢትዮጵያዊነታችን መሪዎቻችን ሕገ መንግስቱንና የተፈጠሩ ስርዓቶችና ሕጎችን በአገሪቱ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ አክብረው እንዲሰሩ አበክረን መጠየቅ ይገባናል። የፕሬዚዳንቱ ወይም የጠ/ሚሩ ልጅ ወይም ዘመድ ወይም ጓደኛ ሙሰኛ ከሆነ (በህጋዊ መንገድ ከተረጋገጠ) እንዲታሰሩ አበክረን ልንጠይቅ ይገባል።

መሪዎች ከሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ይመጣሉ። እንዲሁም በከፍተኛ ሥልጣኖች አብረዋቸው ለመስራት ከዚያም ከዚህም ከተሰበሰቡ ሰዎች ጋር ይሰራሉ። ስለዚህም ይህ ምርጫ በተመለከተ አንዳች ቁጥጥር ማድረግ አይቻለንም ሆኖም እንዴት ሊመሩን እንደሚገባ ልንወስን ግን እንችላለን። ከአንድ ኢትዮጵያዊ ጋር በማወራበት ወቅት በእውነት በጣም ተስፋ እቆርጣለሁ፤ እሱ/እርሷ ኢህአዴግ ወይም «ወያኔ/ኢህአዴግ» እንዴት ሁሉንም ቁልፍ ስልጣኖች - ጠ/ሚኒስትርነት፣ ሌሎች በሚኒስትርነት ስልጣን የሚያዙ ስፍራዎች፣ የጦር አዛዥነት፣ የደህንነት ኃላፊዎች፣ ዲፕሎማሲያዊ ሥልጣኖች ወዘተ - በብቸኝነት እንደያዘ ያወሩኛል። እኔም፣ ለራሳቸው በጎ ነው ብዬ እመልሳለሁ። እነርሱ ኢትዮጵያውያን ናቸውና በመሆኑም በአገራችን የአመራርነት ስፍራ የመያዝ መብት አላቸው። ከማርስ አይደለም የመጡት። የውጭ ወራሪዎችም አይደሉም። በ19ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ አካባቢ በንጉሰ ነገስት ምንልክ ወይም ወደ አብሲኒያ ኢምፓየር በጉልበት ከተቀላቀልነው ከደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ ወይም ደቡብ ምዕራብ ከሆንን አንዳንዶቻችን እንደውም የበለጠ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። ትግሬዎችን የተወሰኑ አብሲኒያውያን በአራት ኪሎ የሚገኘውን የምንልክ ቤተ-መንግስት የቀሟቸው «የውጭ ወራሪዎች» አድርገው ይወስዷቸዋል።

ጠ/ሚ መለስ በፖለቲካ ሹሞቻቸው ደስተኛ ከሆኑ ሌላው ስለምን ሊጨነቅ ይገባል? ማወቅ የምፈልገው በጣም ቀላሉ፣ በመጀመያ ደረጃ የተመረጡት በፍትሐዊ፣ ነፃና ተዓማኒ ምርጫ ነው? እንደገና፣ የሕውሓት/ኢህአዴግ ካድሬ ወይም ባለስልጣን ሙሰኛ ሊሆን ይችላል? ስርዓቱስ እሱን/እርሷን ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ሊወስድ/ልትወስድ ይችላል/ ትችላለች? በኢትዮጵያ ያሉ የፍትህ አካላት /ፍርድ ቤቶች/ ይህን ባለስልጣን የሚዳኙት ከሌላው ዜጋ እኩል ነው? ወይንስ አንድ አይናቸውን የመሸፈን አዝማሚያ አላቸው? እና እርሱ/እርሷ በነፃ ታጅበው ይወጣሉ? የመጨረሻው ጥያቄዬ መቼም አውን ከሆነ ማማው ላይ በተቀመጠው መሪ ላይ ብቻ ሳይሆን መሪው በወጣበት ጠቅላል ብሄር ላይ እጅግ ጠርዝ የደረሰ ጠላትነትና እርኩስ ጥላቻ በሺህዎች እጥፍ በእርግጥኝነት ይፈጠራል:: የመጣው መጥቶ ይህ መቀረፍ አለበት:: አስፈላጊው ሕጋዊና ተቋማዊ መጠበቂያዎች መተግበራቸው ነው:: መሰል ያልተገቡ ተግባሮች ካለጥርጥር ሕዝባዊ ቁጣ/ተቃውሞ እና አለመረጋጋት ማስከተላቸው አይቀርምና::

ውጤታማና የሚተገበር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ መፍጠር ሁላችንም እንደኢትዮጵያዊነታችን የምንችለውና ማሸነፍ ያለብን ጦርነት ነው:: ሆኖም፣ የሰሜን ተወላጅ ጠ/ሚ ቁልፍ ስልጣኖችን ለራሱ ደህንነት ሲል የሰሜን ተወላጆችን እየሾመና እየቀጠረ? ጭራሽ አያስቡት:: ምክንያቱም ወደ ፊት ጠ/ሚር መለስን አማራ ወይም ኦሮሞ ወይም ሌላ የትኛውም ብሄር ተወላጅ የሚተካቸው ቢሆንም እንደእርሳቸው ማድረጉ የማይቀር ነው:: እድሜ ልክ የሚከሰት ነውና:: በመላው ዓለም በሚገኙ በርካታ አገሮች በየዕለቱ እየተከሰተ ያለ ነው ያ:: ከጥቂት ዓመታት በፊት በካናዳ ኦታዋ አብዛኞቹን ከፍተኛ ሥልጣኖች የተቆናጠጡት የኩቤክ ፈንሳይዋን ነበሩ፤ በካናዳ ሕዝብ በነፃ ምርጫ የተመረጡ ራሳቸው ኩቤካዊ ከሆኑ ጠ/ሚ ጋር ወደ ስልጣን የመጡ:: ያን በተመለከተ ካናዳውያን ቅሬታቸውን አስደምጠዋል? በጭራሽ:: ግና የጠ/ሚኒስትሩ ልጅ ሙሰኛ ቢሆን ኖሮና በካናዳ ፖሊሲ ባይያዝ በእጅጉ ተቃውሞአቸውን ያስደምጡ ነበር::

በመጨረሻ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰብዓዊ መብቶች እና ለሕግ የበላይነትና ለገበያ ኢኮኖሚ የሚደረግ ትግል ስር ሰዶ ፍሬ ከማፍራቱ አስቀድሞ ረዥም ጊዜ መወሰዱ አይቀርም:: ምክንያቱም እነዚህን «እስቴቶች» ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትና አዲስ ይዘት መስጠት አሁን ድረስ በጣም አስቸጋሪ ነው:: አዲስ ቴክኒኮችን መማር ወይም አዲስ እውቀት መገብየት ይቻላል፣ ሆኖም የአንድ ማህበረሰብ የሆኑ መጤ «እስቴች» ላይ ባህሪን ከራስ-ማዋሀድ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው:: የማህበረሰቦች መሰረታዊ እሴቶች የሚመነጩት በሂደት ነው፤ እናም አዲስ የሆነ እሴት በማህበረሰብ ውሰጥ እንደአዲስ ማስተዋወቅ ተፈጥሮአዊ የተለመዱ ተቃውሞዎች/ፈጣን ምላሾች ማስከተሉ አይቀርም::

ከሁሉም በላይ፣ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚደረግ (የሚካሄድ ትግል በራሱ እንደመደምደሚያ) ውጤት ተደርጎ ሳይሆን፣ ለድምዳሜ /በመጨረሻ ውጤት/ ወንድ ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት፣ ውጤቱም ትክክለኛ፣ ተግባራዊ (ፊዚካል)፣ ሕዝባዊ ማዕከላት ያለው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞችን ውጤታማነት እነዚህን ለመተግበር የጠቅላላውን ማህበረሰብ «ማህበራዊ ዋስትና» (ዌልፌር)እና መሻሻል ያሰፍናል/ያመጣል::

በአጠቃላይ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ያለውን ጉልህ እውነታ ያጤንን እንደሁ:- ተቀዳሚ ጠላቶቻችን ድህነት፣ በሽታ፣ መጠነ-ሰፊ ስራ-አጥነት፣ የመልካም አስተዳደር እጥረት፣ ፈርጣማ (ጠንካራ) የሕግ

የበላይነት እና ዴሞክራሲ አለመኖር /መታጣት/፣ እና በአሁኑ ወቅት፣ በበርካታ የአገራችን ክፍሎች በብዙ ሚሊዮኖች መካከል ያለው የምግብ እጥረት እና ረሃብ ናቸው:: አስቀድሜ አጽንኦት እንደሰጠሁት፣ ከእነዚህ ሌላ ጠላቶች የለንም እናም ተጨባጭም ሆነ የተሰቡ ተጨማሪ ጠላቶችን ለራሳችን ለመፍጠር ከመታተር (ፍራት) እስኪ እንታቀብ:: አገዛዞች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ፣ አላፊ ናቸው:: ተስፈኛ ነኝ አገር ኢትዮጵያ ሕዝቦቿ ሁሌም ኗሪ ናቸው:: ለአገራችን እና ለሕዝቦቿ የተሻለ መጭ ጊዜ እስኪ እንጣር::

በዲያስፖራ ያለነው ደግሞ፣ ከቻይናውያን፣ ከአይሁዳውን ከሕንዳውያን፣ ከኮርያውያን፣ ከታይዋንያውያን፣ ከአሜሪካውያን ወዘተ ለመማር እና አገር ቤት ለሚገኙ ቤተሰቦቻችን ጥረን ያገኘ ነውን ገቢ ለመላክ ብቻ ሳይሆን በጣም የሚፈለገውን ቴክኖሎጂ፣ የሙያ ስልጠናዎችን (እውቀት)፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ እና አስተዳደራዊ እውቀት (ንቃተ ህሊና) እትብታችን ወደተቀበረበት የትውልድ አገራችን ለማሸጋገር ለራሳችን ቃል-መግባት እና ያለው የፖለቲካ ሥርዓት የፈለገ ቢሆን እና ለአንተ ተቀባይነት የሌለው ቢሆን እንኳ አዎንታዊ እና ገንቢ ውጤት (አስተዋጽኦ) ለማምጣት መጣር ይቻላል::

**ተስፋዬ ሀቢሶ፣በደቡብ አፍሪካና በዩጋንዳ የቀድሞ የኢትዮጵያ አምባሳደር ነበሩ/**

# የፖለቲከኞቻችን አንዱ መገለጫ- ጀብደኝነት!

**በአስቻለው በላይ**

የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን የዓለም ግማሹ ክፍል ርዕዮተ-ዓለም በነበረውና ዛሬም ድረስ ሐገራችንን ጨምሮ በበርከታ አገራት በይፋም የሽፋን ስም እየተሰጠውም የሚቀነቀነው የሶሻሊዝም ምሁራን ጀብደኝነትን «ተጨባጭ ሁኔታዎችን በሚገባ ሳያጤኑ አስፈላጊ ያልሆኑ ችኩል እርምጃዎችን መውሰድ ወይም በውል ያልተጤኑ የኃይል እርምጃዎች እንዲወሰዱ የመገፋፋት አፍራሽ አዝማሚያ ነው:: በተለይ በመደብ ትግል ሂደት ውስጥ ጀብደኝነት በዘፈቀደ እና በስሜት ብቻ በመዋጥ የሚወሰድ አቋም በመሆኑ እጅግ አደገኛ ከመሆኑም በላይ የተስተዋለንና የተቀነባበረን አብዮታዊ የትግል ስልት ይፃረራል» በማለት ይገልፁታል:

በአገራችን ከትናንት እስከ ዛሬ ያልተማሩም የተማሩም በሚባሉ ወገኖች የተካሄዱ የፖለቲከ እንቅስቃሴዎችን ስንቃኝ በአብዛኛው የምናገኘው ድርጊት ከላይ ትርጓሜው የተገለጸውን ጀብደኝነት የሚያሳይ ነው::ከእኔ በላይ ላሳር፣ማን ደፍሮኝ፣ወዘተ የሚሉት አስተሳሰቦች በአድራጊዎቹ ወገን «እሰረው አስወግደው አባረው ወዘተ» የሚሉት አፍራሽ ምክሮች ደግሞ ዙሪያ ከበው ከሚያጨበጭቡት በኩል መሰማት የፖለቲካችንና የፖለቲከኞቻችን መገለጫዎች ናቸው:: ትናንትም ሆነ ዛሬ- ውጤቱ ደግሞ ጥፋት::

ከተፈጸመው ይልቅ ወደፊት ስለሚሆነው በማሰብ በሀሳብ የሚለዩዋቸውን አይደለም ጦር አዝምተው የተዋጉዋቸውንና ሥልጣናቸውን የተቀናቀኑዋቸውን «ባላንጣዎቻቸውን»በሰላማዊ አግባብ በማስተናገድ ረገድ ፊደል አልቆጠሩም የሚባሉት አባቶቻችን የዘመናዊነት ከባ ከጠለቀው ትውልድ በእጅጉ የሚበልጡ እንደነበሩ ታሪክ ለትውልድ ያቆየው ታሪካቸው ይመሰክራል:: ጦርነት ገጥመው ያሸነፉትንና በምርኮ የያዙትን መልሰው ሹመት ሰጥተው ከክብር ቦታ በማስቀመጥ ቂም እንዳይኖር ቁርሾ እንዲጠፋ የማድረግ ሥራቸው በዚህ ዘመን የማይታሰብ የፖለቲካ ጥበብ ነው::ከራስ በላይ የማሰብ፣ከዛሬ ይልቅ ስለ ነገው በጎ ራዕይ የመሰነቅ አስተውሎት ውጤት ነው:: በዚህ ረገድ ዕምዬ ምንይልክ በቁጥር አንድ ይጠቀሳሉ::

በታሪካችን ውስጥ ትልቅ ጠባሳ ጥሎ ያለፈውና ከትውልዱ አእምሮ ውስጥ ለዝንተ ዓለም ሊጠፋ የማይችለው «የአባላሸኝ ዘመን»ድርጊት በሙሉ የጀብደኝነት ውጤት ነበር ማለት ይቻላል::ማመዛዘን የጠፋበት ረጋ ብሎ ግራና ቀኙን ለማስተዋል ትእግስት የጎደለበት በሀሳብ ቀርቶ በቃላት በሚፈጠር ልዩነት ቃታ የሚሳብበት የተለየ መስመር ይከተላል ከእኛ በተቃራኒ የሆነ አመለከከት ያራምዳል ያሉትን አባት እናት እህት ወንድም ሳይሉ መግደል እንደ ጀብዱ የታየበትንና በጀግንነት የተቆጠረበትን ጀብደኝነት የነገሰበት ወቅት አሳልፈናል::

ታሪክ ስልጣን የመያዝ አጋጣሚውን የሰጠው ወታደራዊው ደርግ አባላት ከሌሎች በአመለከከት ከሚለዩዋቸው ጋር ለመወያየት ቀርቶ በራሳቸው መከከልም ተወያይቶ ለመግባባት ተቻችሎ ሥልጣን ለመጋራት ጀብደኝነታቸው አላስችል ብሏቸው ራስ በራሳቸው ሲጠፋፉ አገሪቱንም ሲያጠፉ ኖረው አይወድቁ አወዳደቅ ወደቁ::ደርግን ተቃውመው የተሰለፉትም ወገኖች እንቃወመዋለን የሚሉትን የታጠቀ ኃይል ከፊት ለፊታቸው አስቀምጠው ልዩነቶቻቸውን በውይይት አጥብበው በመቻቻል ተደጋግፎ ለመንጓዝ ጀብደኛ ባህሪያቸው አላበቃ ብሏቸው ፓርቲ ከፓርቲ ብቻ ሳይሆን በአንድ ፓርቲ ውስጥም የፈጠሩት መተላለቅ ሊረሳ የሚችል አይደለም::አሳዛኙ እና አሳፋሪው ነገር ደግሞ ከዚህ መማር ያለመቻሉ ነው::

የሂደቱ አካል የነበሩት የይድረስ ለባለ ታሪኩ መፅሐፍ ፀኃፊ «ሁላችንም በተዘዋዋሪ መንገድና ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ሲበዛ ለድርጅት ሲያንስ ለግል ስልጣን ሽኩቻ ስንባላ ለዚያው ተመሳሳይ ዓላማ የቆሙት ኮ/ል መንግሥቱ በአሽናፊነት ሊበሉን በአንድ ቦታ አሰባሰቡን::ክቡር በሆኑ የሕዝብ ጥያቄዎች ላይ ካደረስነው በደል አንፃር ከዚህ የበለጠ ምን የታሪክ ፍርድ ይኖራል?» በማለት የገለፁት የወቅቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ጀብደኝነት የተጠናወተው እንደነበረ የሚያሳይ ነው::

ሌላው የወቅቱ ሂደት ባለ ድርሻ የነበሩት አቶ አሰፋ ጫቦ ብዕራቸው እንደ ዛሬ ከመንጠፉ በፊት በተለያዩ የህትመት ውጤቶች ላይ ሲያቀርቧቸው በነበሩ ማራኪና ተነባቢ ፅሁፎች «ከዛ የአባላሸኝ ዘመን ድርጊት ማንም ነፃ ሊሆን አይችልምና ሁላችንም የድርሻ የድርሻችንን እንውሰድ » ብለው ነበር::ይህ ሀሳብ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ራስን ወይንም የነበሩበትን ድርጅት ነፃ ለማድረግ ሌላኛውን ወገን ከመወንጀል አስተውሎት የጎደለው ጀብደኛ ድርጊት በመላቀቅ ሁሉም የድርሻ የድርሻውን ተጠያቂነት በሌሎች አስገዳጅነት ሳይሆን በራስ የህሊና ውሳኔ መውሰድ ቢችል ተከታዩም ከዛ በመማር ከጀብደኝነት ፖለቲካ በተላቀቀ ከመከዳዳት እኩይ ተግባር በተለያየ ነበር::ነገር ግን

የትናንቱ ድርጊት ትክክለኛ የታሪክ ፍርድ አላገኘምና የሂደቱ አካል የነበሩት ራሳቸውንና የነበሩበትን ድርጅት ነጻ አድርጎ ሌላኛውን በመወንጀል ያንኑ የጀብደኝነት ተግባር ዛሬም ሲቀጥሉበት አዲሱም ያንኑ እየተማረ ያዘግማል፡፡

ሌላውን ለማውገዝና ለመወንጀል እንጂ ራሳቸውን ለማየት የማይደፍሩት ፖለቲከኞች ከትናንት ይዘውት በመጡት ወይም ከታላላቆቻቸው «በተማሩት»መንገድ የሚጓዙ በመሆናቸው ነው ሁለተኛው «አብዮት»በኢትዮጵያ ከፈነዳበት ከ1983 ዓም ጀምሮ አገራዊ ለውጥ ቀርቶ የግለሰብ ፖለቲከኞች የአስተሳሰብ ለውጥ ማየት ሳንችል የመጀመሪያውን አብዮት ዕድሜ ያስቆጠርነው፡፡

የሁለተኛው «አብዮት»ባለቤት የሆነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ አራማጁ ወገንም ያለፈውን አብዮት ሂደት ሲያወግዝና አብዮተኞቹም ላይ እርምጃ ሲወስድ እነርሱን የወነጀለበትን ተግባር ከመፈጸም ግን አልታቀበም፡፡ውይይት የለ እርምጃ፣ መቻቻል የለ፣ ፍረጃ የተቃወመ ሁሉ ጠላት፡፡ በሀሳብ የተለየ ሁሉ ፀረ ሠላም፡፡ ነገሩ ሁሉ በእርጋታ ሳይሆን በእልህ፣በአስተውሎት ሳይሆን በጀብደኝነት የሚፈጸም ሆኖ ዛሬም ዴሞክራሲ እንደናፈቀን እንገኛለን፡፡

ግልፅ መስመርና የዓላማ ልዩነት ባላቸው በገዢውና በተቀዋሚ ፓርቲዎች መካከል ቀርቶ በአንድ ፓርቲ ውስጥ የተሰባሰቡት እንኳን ልዩነቶቻቸውን በውይይት የሚያስታርቁ የተለያየ አመላቸውን በመቻቻል የሚያስተናግዱ ነገሮችን በእርጋታ ጊዜ ሰጥተው የሚመለከቱ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በሚገባ አጢነው የሚወስኑ ሆነው የታዩበትን ጊዜ ማስታወስ አይቻልም፡፡

የፓርቲ ሥልጣን የተቆናጠጡ ቢሮ ከማህተም የጨበጡ ወገኖች እነርሱ ከሚፈልጉት በተቃራኒ የሆነን ሀሳብና ተችት ከተጨባጩ እውነታ ጋር አገናዝቦ ለመመልከት ጀብደኛ አቋማቸው የማይፈቅድላቸው ሆኖ ነው ከዓመት ዓመት በየፓርቲዎቹ ውስጥ ሰርጎ ገብ፣አፍራህ፣አንጃ፣ወዘተ የሚሉት ቃላት የሚሰሙትና ማገድና ማባረር ዋንኛ ሥራቸው ሆኖ የሚታየው፡፡ከዚህ በላይ ለማድረግ ወቅቱ የማይፈቅድ መሆኑ በጀ እንጂ እንደ አንዳንዶቹ አያያዝ የትናንቱ መተላለቅ ዛሬም ይደገም ነበር፡፡ለነገሩ የራስን ፓርቲ አባል በመንግስት ከሚፈለግ ድርጅት ጋር ማነካካት ከመግደል አይተናነስም፡፡

ሁለተኛው «አብዮት» ባስቆጠረው 17 ዓመታት የውስጥ ልዩነቶቹን በውይይት ፈታ ተብሎ የሚነገርለት ፓርቲ የለም፡፡ይልቁንም ልዩነታችሁ ምንድን ነው ችግራችሁን ለምን በውይይት አትፈቱትም ተብሎ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ሁሌም በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይ ነው፡፡የሚቃወሙን ጥቂቶች ናቸው፣ሰርጎ ገቦች ናቸው፣ ፓርቲ የማፍረስ ተልኮ ያላቸው ናቸው፣ ወዘተ የሚሉ መልሶች ናቸው የሚሰሙት፡፡

የልዩነቱ ሀሳብ ተገልፆ ትክክለኛ አይደለም የተባለበትና አፍራሽ ለማሰኘት የበቃበት ምክንያት በማስረጃ ተዘርዝሮ አይቀርብም፡፡እዚህ ላይ ከተናጋሪዎቹ ድፍረት የአድማጩ ተቀባይነት ያስገርማል፡፡በዚህ የመረጃ ዘመን ማስረጃ ያልቀረበበትን «ሾላ በድፍን»የሚገለፅ ነገር ከመስማት አልፎ መቀበልና ማመን አልፎ ተርፎም ማራባት ራስን ያለመሆንና የጀብደኞች መሳሪያ ሆኖ መሰለፍ ነው፡፡ጀብደኞችን የሚያበረታታቸውና የለየለት አንባገነንነት ደረጃ የሚያደርሳቸው ለመረጃ ሳይሆን ለአሉባልታ ልቡን የሚሰጥ ለዓላማ ሳይሆን ለጥቅም የተሰለፈ ደጋፊ በዙሪያቸው መበራከት ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተገለጸው ድርጊት ሰሞነኛ ባለቤት አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሆኗል፡፡ፓርቲው በተመሰረተ ሰሞን ከትናንት ተምረናል የሚለው ቃል ዘወትር ከአመራሮቹ የሚደመጥ ነበር፡፡ በአዲስ አስተሳሰብ የአዲስ ምዕራፍ ጉዞ ጀምረናል ሲሉም ነግረውን ነበር፡፡ይህም በብዙዎቻችን ዘንድ እነዚህ በምርጫ 97 አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በእስርም የተንገላቱ የአንድነት አመራሮች ከሩቁም ሆነ ከቅርቡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተምረው በ97ቱ ምርጫ ምክንያት በእጅጉ የተጎዳውን ሕዝብ የሚክስ ተግባር ያከናውናሉ የሚል ተስፋ አጭሮ ነበር፡፡

ፓርቲው አዋሳ ላይ ባደረገው ሕዝብዊ ስብሰባ ላይ «ልዩነቶቻችሁን ለምን በውይይት አትፈቱም?» ተብሎ ከተሰብሳቢው ለተነሳ ጥያቄ የአንድነት ም/ል ሊቀመንበር የሆኑት ኢ/ር ግዛቸው የሰጡት ምላሽ ለዓመታት የሰማነውና የተለመደው ነው፡፡«ጥቂቶች ናቸው ፣22 ሰዎች ናቸው፡፡»ነበር ያሉት፡፡ለኢ/ር ግዛቸው ቀጥተኛ ምላሽ ባይሆንም የእለቱ የክብር እንግዳ የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ በተያዘላቸው ተራ ሲናገሩ«ቁም ነገሩ የቁጥር ጉዳይ ሳይሆን የዓላማ ግልፅነትና የዕምነት ፅናት ነው»በማለት ተሞክሮአቸውን ሲናገሩ አብዛኛው የስብሰባው ታዳሚ ከቀዳሚው የኢ/ር ግዛቸው ምላሽ ጋር በማነጻጸር አግራሞቱን በሳቅ ገልጿል፡፡

በመግቢያዬ ላይ የገለፅኳቸው የሶሻሊዝም ርዕዮት አራማጅ ምሁራን ጀብደኝነት «የሰፊውን ሕዝብ የቅርብና የሩቅ ጊዜ ግቦች በትክክል ያገናዘበ ባለመሆኑ በረጅም የትግል ሂደት ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን ድል በፍላጎት ብቻ በመገፋፋት ዛሬውኑ ለማከናወን ያልማል፡፡በዚህም ሰፊውን ህዝብ ጭምር ወቅቱና ሁኔታው ባልፈቀደው ፍልሚያ ውስጥ በመዝፈቅ ለጥፋት የሚዳርግና አብዮታዊ እንቅስቃሴንም በአድሃሪያን የሚያስመታ በመሆኑ ኮሙኒስቶች በፅኑ ይታገሉታል»በማለት ያብራሩታል፡፡

በዚህ መልኩ የተቃውሞ ፖለቲካው መሪዎች ጀብደኝነት የተጠናወታቸው ከሆኑ እንዴት ነው ለመንግስትነት ሥልጣን ልናስባቸው የምንችለው?በፓርቲያቸው ውስጥ መቻቻልን የመፍጠር ብቃት፣ ውይይትን የማከሄድ ድፍረት፣ ነገሮችን በእርጋታ የመመርመርና አስማሚ መፍትሄ የማምጣት ችሎታ ከሌላቸው ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም የሚያስቡ ለሥልጣናቸው ሳይሆን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚጨነቁ ካልሆኑ እንደምን ለመሪነት ልናጫቸው ይቻለናል?ከመጥበሻው ወደ እሳቱ !

ተጨባጭ ሁኔታዎችን በሚገባ ሳያጤኑ አስፈላጊ ያልሆኑ ችኩል እርምጃዎችን የመውሰድና በውል ያልተጤኑ የኃይል እርምጃዎች እንዲወሰዱ የመገፋፋት አፍራሽ አዝማሚያ የሚንፀባረቅበት ከየትኛውም ወገን የሚታየው ጀብደኝነት አገራችንን ዛሬ ላለችበት ደረጃ አድርሷታል፡፡ይህ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ መልካም ነው፡፡ለነገውም ብሩህ ተስፋ ፈንጣቂ ነው የሚል ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ዜጋ ካለ የራሱን ደሴት ፈጥሮ የሚኖር መሆን አለበት፡፡

የማናቸውንም ሰው ቀልብ የመሳብ አቅም ካላቸው ሕንፃዎች በስተጀርባ የሰው ልጅ የሚኖርባቸው የማይመስሉ ቤት ተብዬዎች የመኖራቸውን ያህል በአደባባይ ከሚነገረው ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ልማት፣ እኩልነት ወዘተ በስተጀርባ ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ይህን ለማወቅ ደግሞ ከህንፃው ጀርባ ዞሮ መመልከትን ከሚነገረው በተቃራኒ ያሉ እውነታዎችን መመልከትን ይጠይቃል፡፡

ስለሆነም ሀገራችን ልጆቿ በእኩልነት ሰርተው የሚበለፅጉባት በኩራት የሚኖሩባት ለነገው ትውልድ ብሩህ ተስፋ የሚታይባት የሚሰደዱባት ሳትሆን በፍቅር የሚኖሩባት ትሆን ዘንዳ ማስተዋል ከጎደለውና ችኮላ ከሚያጠቃው ለውይይት ሳይሆን ለእርምጃ ቅድሚያ ከሚሰጠው ጀብደኝነት መላቀቅ ያስፈልጋል።ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥቅምት 23 ቀን 1935 ዓም ለፓርላማ አባላቱ«የሚመከረው ነገር ሁሉ በዝግታና በጥልቀት ታስቦ በለዘብታ ክርክር ተጣርቶ በትዕግስት እየተመላለሰ ተመክሮ የተቆረጠ ነገር እንዲሆን ነው።»በማለት የተናገሩትን መሪ ቃል በፓርቲም ሆነ በአገር ደረጃ ተቀምጠው የሚወስኑ ሰዎች ቢያስተውሉት።...

## ሞቲቬሽን

# *መንታ ስሜቶች*

***«ሀዘንን ያልተመለከተ ደስታን ሊያይ አይችልም»***

***ካህሊል ጆብራን***

በየሁሉም ሁኔታ ውስጥ ተቃራኒ ነገሮች ሁልጊዜ ያገኛል። ያየነው፣ ያዳመጥነው እና እየተከተልነው ያለው ነገር አንድን ነገር ከሆነ እዛ ነገር ላይ በጣም «ቢዚ» ስለምንሆን ምናልባት የዛን ነገር ተቃራኒ የሆነ ነገር ልናይ አንችልም። ብናይም በስራ ስተጠመድን ልናዳምጠው አንችልም። የማስተዋል ነገር ነው እንጂ ሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች ሁሌም አሉ። ለዛ ማረጋገጫ የሚሆነው ሕይወትን በመመልከት ነው። ብርሃን እንዳለ ሁሉ ጨለማ አለ። መውደቅ እንዳለ ሁሉ መነሳት አለ። ደስታ እንዳለ ሁሉ ሀዘን አለ። ያሰብነውን ነገር ማሳካት እንዳለ ሁሉ አለማሳካት አለ። እንደዚህ በተቃራኒ አቅጣጫ ላይ የሚጓዙ ነገሮች መኖራቸው በራሳቸው ምንም ችግር የላቸውም። ግን አንድ ለእኛ የማይጠቅመን ወይ የማያስደስተን አቅጣጫ ላይ ሆነን በዓለም ላይ የሚገኘው አቅጣጫ ያ ብቻ ነው ብለን ካሰብን ነው። እንደዚህ ስናስብ ዘወር ብለን ህይወትን ማስተዋል አለብን። ፀሐይ ማታ እንደምትገባው ጠዋት ተመልሳ ትወጣለች አይደለምን? ማታ በጨለማ ተኝተን አድረን ጠዋት ስንነሳ ብርሃን አይደለም የምናየውን?

እውነት ተፈጥሮ እንደዚህ ባይሆን ኖሮ ብዙ ነገሮችን ዋጋቸውን አናይም ነበር። ለምሳሌ ጨለማ ባይኖር እንዴት ብለን ብርሃንን እንናፍቃለን? ብርሃን ትርጉሙን ያጣል። ደስታን ስናገኝ እና ስንደሰት የበለጠ ደስታ የሚሰጠውን ስሜት የምንፈልገው ሀዘንን ስለምናውቅ ነው። በተለያዩ አጋጣሚዎች የሀዘንን ስሜት እናውቀዋለን፣ ለዛም ነው የዚህን ተቃራኒ የሆነ ስሜት የሚሰጠንን ደስታን ሁሌም ቢሆን የምንፈልገው። ይሄ ባይሆን ኖሮ ግን ደስታም የደስታን ስሜት አይሰጠንም፣ ሀዘንም እንዲሁ። ለዚህም ነው በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ስኬትን ያገኘ ሰው ያ ስኬት የሚሰጠውን ስሜት ከማንኛውም ሰው በበለጠ የሚያውቀው።

ማወቅም ብቻ ሳይሆን የሚያጣጥመው፡፡ ምክንያቱም ስኬቱን ከማግኘቱ በፊት ወድቋል፣ ወዲያ ወዲህ ብሏል፣ ተስፋ ቆርጧል፣ በጥርጣሬ ተከቧል፣ ወዘተ፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚሰጡትን ስሜት ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ስሜቶቹ ያው መጨረሻ ላይ ካገኘነው ስሜት ጋር ጨርሶ አይገናኙም፡፡ ሁለቱም ለየቅል ናቸው፡፡ አንዱ ተስፋ ቁረጥ አንተ ይሄን መስራት አትችልም የሚል ሲሆን በሌላ አቅጣጫ የሚገኘው ስሜት ደግሞ አዎ ይህን ማድረግ ትችላለህ የሚል ነው፡፡ እዚህ ስሜት ውስጥ በራስ ውጤት መደሰት፣ ተስፋ፣ እምነት፣ ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገ ማሰብን፣ የነገሮችን መልካም ጐን ማየትን የመሳሰሉትን ደስ የሚሉ ስሜቶች ያገኛሉ፡፡

እንደዚህ ዓይነት ተቃራኒ ስሜቶች አንድ ላይ በጭራሽ አብረው መኖር አይችሉም፡፡ እንዴት ተደርጐ? በተለያየ አቅጣጫ ላይ የሚገኙ ስሜቶችን አንድ የሚያደርግ ምንም ነገር ቢፈለግ አይገኝም፡፡ ለዛ ነው አንድ ቤት ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች አብረው መኖር የማይችሉት የሚባለው፡፡ አብረው ቢኖሩም እንኳን በሰላም መኖር አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ሁሉ እንደተጣሉ ነውና፡፡ ፍቅር የሚገኝበት ቤት ውስጥ ጥርጣሬ ካለ ምን እንደሚሆን ማሰብ አያዳግትም፡፡ ፍቅሩ ለማደግ፣ ለመብዛትና ለማበብ እየፈለገ እዛው ቤት ውስጥ ጥርጣሬ ስላለ ፍቅር የሚፈልገውን ነገር አያገኝም፡፡ ይህም ማለት እዛ ቤት ውስጥ ያለው ነገር ለፍቅር በጭራሽ አያመችም፡፡ ለዛ ነው ፍቅር እና ጥርጣሬ እንደ ላይ ይኖራሉ ለማለት የማይቻለው፡፡ እንደ አንዳቸው ጥንካሬ አንዳቸው ይኖራሉ፡፡ ቤት ውስጥ የሚገኘው ፈቅር ከጥርጣሬው የሚበልጥ ከሆነ ፍቅር አሸንፎ ተንደላቆ ይኖራል፡፡ በሌላ ጎን ደግሞ ቤቱ ውስጥ የሚገኝ ው ጥርጣሬ ከፍቅር ከበለጠ እዛ ቤት ውስጥ ፍቅር ቦታ የለውም፡፡ ጊዜውን ጠብቆ ፍቅር ለጥርጣሬ እጁን ይሰጣል፡፡ ፍቅርና ጥርጣሬ አንድ ላይ እንኑር ካለ ግን በሰላም ተግባብተው መኖር አይችሉም፡፡ ሁሌ እንደተጣሉ ነው፡፡

**«ጥርጣሬ ህመም ሆኖ በጣም ብቸኛ ከመሆኑ የተነሳ እምነት መንትያ ወንድም እንደሆነ አያውቅም፡፡»**

**ካህሊል ጂብራን**

እኔ ይሄን ማድረግ አልችልም፣ ያ ሊሳካ አይችልም፣ ይሄ እንዴት ይሆናል፣ ይሄንን ልጀምር አልችልም፣ ብጀምርም ልጨርስ አልችልም፣ ብጨርስም ዘለቄታነት አይኖረውም፣ የመሳሰሉትን ስሜቶች ጥርጣሬ በማስተናገድ ስራ ሲበዛበት አጠገቡ የሚገኝን ነገር አያይም፡፡ ቢያይ ኖሮ ጥንካሬው በቀነሰ ነበር፡፡ ሌላ አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሌላ ጠንካራ ስሜት እንዳለ ስለማያስተውል ጥርጣሬ ጥንካሬውን እንደያዘ ይገኛል፡፡ ቆም ብሎ ቢያስተውል ኖሮ አጠገቡ የሚገኝ ሌላ ጠንካራ ተቃራኒ ስሜት አለ፡፡ ያም ስሜት ይሄን ማድረግ ትችላለህ፣ ያንን ከጣርክ ይሳካልሃል፣ ይሄም ሊሆንልህ ይችላል፣ ይሄንን ነገር ጀምረው፣ የጀመርካቸውንም ነገሮች ጨርሳቸው፣ የጨረስካቸውንም ነገሮች ዘለቄታነት ማየት ትችላለህ የሚል ነው፡፡ እነዚህ ስሜቶች እምነትን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

በተለያዩ መንገዶች የሚሄዱ ስሜቶች አይተዋወቁም፡፡ እንተዋወቅም ቢሉ ሊዋደዱ አይችሉም፡፡ ስለዚህ የማንወደው ለእኛ የማይመች ስሜት ሲሰማን ብዙም ሳይርቅ የዛ ተቃራኒ የሆነ ስሜት እንዳለ እናስብ፡፡

# ስፖርት

## ኃይሌ ገ/ሥላሴ ዳግም በበርሊን ነገሰ!

- **በሴቶች አፀደ ሀብታሙ አሸንፋለች**

የዓለማችን የምንግዜም ታላቅ አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ እሁድ ለ36ኛ ጊዜ በተካሄደው ዓመታዊው የበርሊን ማራቶን 2.06.08 በመግባት ለአራተኛ ተከታታይ ዓመት የውድድሩ አሸናፊ ሆነ፡፡ ብቸኛው ሪከርድ ማሻሻል ግን ሳይችል ቀርቷል፡፡

ኢትዮጵያዊው ኮከብ በተከታታይ በተደረጉ ሁለት የበርሊን ማራቶን ውድድሮች ሪከርድ የሰበረ ሲሆን በዘንድሮም ውድድር 30 ኪሎ ሜትሩን ሮጦ ያጠናቀቀበት 1:27.49 የዓለም ሪከርድ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ «አሯሯጤ የተሟላ (Perfect) ነበር፡፡ እስከ 33 ኪሎ ሜትር ድረስ ሪከርድ መስበር በሚያስችል ፍጥነት ላይ ነበርኩ» ያለው ኃይሌ የውድድሩ የመጨረሻ 10 ኪ.ሜ. ሞቃታማ ስለነበር እንዳልተመቸው አስታውቋል፡፡ «የማራቶን የአየር ፀባይ አልነበረም፡፡ በመጨረሻዎቹ 10 ኪሎ ሜትሮች በጣም ሞቃታማ ነበር፡፡ ስንጀምር ግን ጥሩ አየር ነበር፡፡» በማለት የአየር ፀባዩ የሙቀት መጠን እየጨመረ በመምጣቱ ውድድሩን እንዳከበደበት ቢያስታውቅም በውጤቱ ግን ደስተኛ ነው፡፡ «የ30 ኪሎ ሜትር የዓለም ሪከርድ መስበሬን ስታውቅ መጥፎ ውጤት አለመሆኑን ትረዳለህ፡፡ የግል ማህደሬ የውጤት ስብስብ ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ በማሸነፌና ባስመዘገብኩት ሰዓት ደስተኛ ነኝ» ሲል በፈገግታ ተሞልቶ ከነበረው ሞቃታማ የአየር ፀባይ አንፃር ጥሩ ውጤት ማስመዝገቡን ይገልፃል፡፡ ኃይሌ አራት ጊዜ የበርሊን ማራቶንን በማሸነፍ ብቸኛ ሰው ሆኗል፡፡

«ለማራቶን ሩጫ የሚመች የአየር ፀባይ አልነበረም፡፡ ጥሩ ነበርኩ፡፡ በመጨረሻዎቹ ኪሎ ሜትሮች ላይ ግን ተዳክሜያለሁ፡፡ ችግሩ የጀመረው ከ33ኛው ኪሎ ሜትር በኋላ ነው፡፡ ምናልባት ብዙ በመሳቤ ይሆናል፡፡ ልገፋ ብሞክርም በመጨረሻ አምስት ኪሎ ሜትሮች ይበልጥ ደከምኩ፡፡ ከዚያ በላይ ማድረግም አልቻልኩም፡፡» የሚለው ኃይሌ በቀጣይ ሊያሳካቸው የሚታትርላቸው ሁለት ታላላቅ እቅዶች አሉት፡- ባለፈው ዓመት በርሊን ላይ 2.03.59 በመግባት ያሻሻለውን ***የዓለም የማራቶን ሪከርድ ዳግመኛ መስበር*** እና በ2012 በለንደን በሚካሄደው ***ኦሎምፒክ ላይ በመካፈል በማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ ማግኘት***፡፡ ስለሁኔታው ሲገልፅም፣ «ይህ ለኔ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው፡፡» በማለት ነበር፡፡

ማራቶንን ከ2:04 በታች የገባ ብቸኛው የፕላኔታችን ሰው ከበርሊን ሁለት ነገር ቀስሟል፡፡ «ዛሬ (እሁድ) ከተማርኩት ነገር አንዱ የዓለም የማራቶን ሪከርድን ለመስበር የአየር ፀባዩ ከ17 ዲግሪ ሴሊሺየስ ያነሰ ወይም እስከ ከ17 ዲግሪ ሴሊሺየስ መሆን እንዳለበት ነው፡፡» ሁለተኛውን ነጥብም ይናገራል፡- «ሌላው ዛሬ የተማርኩት፣ ማራቶን በትክክለኛው መልኩ የሚጀመረው ከ35 ኪሎ ሜትር በኋላ መሆኑን ነው፡፡»

ኃይሌ ባለፈው ዓመት ባስመዘገበው የሪከርድ ሰዓቱ 2:03.59 ዘንድሮ የሮጠው 41.71 ኪሎ ሜትር ነው:: የገባበት 2.06.08 ከዓለም ሪከርድ ሁለት ደቂቃ ከዘጠኝ ሰከንድ የራቀ ነው::

ኬንያዊው ፍራንሲስ ኪፕሮፕ ከኃይሌ 58 ሰከንድ በኋላ በመግባት ሁለተኛ ሲወጣ ኢትዮጵያዊው ነጋሪ ተርፋ 2.07.41 በመግባት ሶስተኛ ሆኗል:: ከኃይሌ ቀጥሎ በሮተርዳም ማራቶን የዓመቱን ፈጣን የማራቶን ሰዓት ያስመዘገበው ኬንያዊው ዱንካን ኪቤት የኃይሌ ተፎካካሪ ይሆናል ተብሎ ቢጠበቅም ምንም መፍጠር ሳይችል ከ30 ኪሎ ሜትር በኋላ አቋርጦ ሊወጣ ችሏል:: ለውድድሩ የ2007 የኦሳካ የዓለም አትሌቲክስ አሸናፊው ኬንያዊው ሉክ ኪቤት አሯሯጭ የነበረ ሲሆን አቋርጦ ከመውጣቱ በፊት ኃይሌ 20ኛው ኪሎ ሜትር ላይ አልፎት ሄዷል::

በሴቶች ኢትዮጵያዊቷ አፀደ ሀብታሙ 2:24.47 በመግባት አሸንፋለች:: ራሺያዊቷ ሲልቪያ ስክቮርትሶቫ በ2:26.24 በመግባት ሁለተኛ ወጥታለች:: ሌላዋ ኢትዮጵያዊት ማሚቱ ዳስካ በ2:26.38 ገብታ ሶስተኛ ሆና ውድድሯን ፈጽማለች:: አምና የውድድሩን አሸናፊ ኢሪና ሚኪቴንኮን ተከትላ ሁለተኛ የወጣችው አስካለ ጣፋ ለአሸናፊነት ግምት ተሰጥቷት የነበረ ቢሆንም ከውድድሩ አቋርጣ ወጥታለች::

የውድድሩ አሸናፊዎቹ ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች 50 ሺህ ዩሮ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል:: ኃይሌ ከ2 ሰዓት ከ6 ደቂቃ ከ30 ሰከንድ በታች ለገቡ ወንድ አትሌቶች የሚሰጠውን ተጨማሪ 30 ሺህ ዩሮ «ቦነስ» ማግኘት ችሏል:: አፀደ 2 ሰዓት ከ21 ደቂቃ ከ30 ሰከንድ በታች መግባት ብትችል ኖሮ ተጨማሪ 30 ሺህ ዩሮ ማግኘት ትችል ነበር::

ከ122 ሀገሮች የተውጣጡ 40 ሺህ 9መቶ 23 ተሳታፊዎች የተካፈሉበት የበርሊን ማራቶን (ቁጥሩ ሪከርድ ነው) ውድድርን፣ 1 ሚሊየን የሚጠጉ ሰዎች በመንገድ ላይ ተከታትለውታል:: በርሊን ላይ እስከ 20 ዲግሪ ሴሊሺየስ የተመዘገበ የአየር ፀባይ ነበር::

# የቅ/ጊዮርጊሱን የቀድሞ ተጨዋች [ተስፋዬ ኦርጌቾን] የመታደግ ጉዞ

**የኢትዮጵያ ብ/ቡድንና የቅ/ጊዮርጊስ የቀድሞ ተጨዋች የነበረው ተስፋዬ ኦርጌቾ በችግርና በህመም ሳይ ይገኛል:: ህይወቱንም ለመታደግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: ከተስፋዬ ጋር ቆይታ ያደረገው የአውራምባ ታይምስ የስፖርት ገጽ አዘጋጅ ተጨዋቹን እንዴትና ለምን መርዳት እንደሚገባ በቀጣዩ ፅሁፍ ያሳያል::**

ተስፋዬ ኦርጌቾ እግር ኳስን መጫወት የጀመረው በተወለደባት ወንጂ ከተማ ውስጥ ነው:: ከልጅነቱ አንስቶ የሚያዘወትረውን እግር ኳስ የትውልድ ከተማው ቡድን የሆነው ወንጂ ስኳርን በ1981 ዓ.ም. በመቀላቀል የክለብ እግር ኳስን ተዋወቀ:: በወንጂ ስኳር የሁለት ዓመት ቆይታው የነበረው እንቅስቃሴ አይን ውስጥ እንዲገባ አደረገው:: በአጨዋወቱ ምራቃቸውን የዋጡ ክለቦች የተጫወትልን ጥያቄዎች ያጉርፉለት ጀመር:: ለምስራቅ ሸዋ ምርጥ ቡድን ተመርጦ በአዲስ አበባ ስታዲየም ሲጫወት የተመለከቱትማ አጭሩን የአማካይ ስፍራ ተጨዋች ላለማጣት ፉክክሩን አጦፉት:: የምስራቅ

ሸዋ ምርጥ አሰልጣኝ የነበሩት ሐጐስ ደስታ ተጨዋቹን በቅርብ ማግኘታቸው አሳምነው በክለብ ደረጃ ወደ ሚያሰለጥኑት አየር ኃይል ለመወሰድ የተሻለ እድል ነበራቸው፤ አደረጉትም፡፡

1983 ዓ.ም. ኢህአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት ወቅት ነው፡፡ በከተማዋ በነበረው አለመረጋጋት የተነሳ ውድድሮች ተቋርጠው ነበር፡፡ ይህም የተስፋዬ የአየር ኃይል ቆይታ በስምንት ጨዋታዎች ላይ ከመገኘት የዘለለ ሚና እንዳይኖረው አደረገው፡፡ ወንጂ ስኳር ሲጫወት አንስቶ በትኩረት ይከታተለው የነበረው የቅ/ጊዮርጊስ ቡድን ወንጂ ድረስ አሰልጣኙ መንግስቱ ወርቁን በመላክ አነጋገረው፡፡ ተስፋዬም ደስተኛ በመሆኑ በ1984 ዓ.ም. የቢጫና ቀዩ መለያ አባል ሆነ፡፡ ገ/መድኃን ኃይሌና ሙሉጌታ ከባደን የመሳሰሉ ተጨዋቾች የነበሩበትን ስብስብ ሲቀላቀል ብዙ መስራት እንደሚጠብቀው ተረዳ፡፡ «የመጀመሪያ ጊዜ ከእረፍት መልስ ተቀይሬ ገብቼ በስታዲየሙ የነበረውን የደጋፊዎች ሁኔታ ስመለከት ለዚህ ክለብ ብዙ ማድረግ እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ ደጋፊዎችን ሳገኝ፣ መገናኛ ብዙሐኖችን ስከታተል በይበልጥ የክለቡን ታላቅነት ተረዳሁ፡፡ ራሴን ለማሳወቅና ክለቤን ለመጥቀም አሰልጣኜ ከሚሰጠኝ ልምምድ በተጨማሪ በግሌ እሰራ ነበር» ይላል የነበረውን በቶሎ የማደግ ፍላጎት ሲገልፅ፡፡ ተስፋዬ አብረውት ከተጫወቱ ተጨዋቾች መሀከል ሙልጌታ ከበደን ያስቀድማል፡፡ ስለ ሙልጌታ ሲገልፅ በደስታ ተሞልቶ ነው፡፡ «በእኔ ዘመን የተመለከትኩት ታላቅ ተጨዋች ነው፡፡ መቼም ቢሆን መሸነፍ አይወድም፡፡ ከሜዳ ውጪ ባለው ህይወቱም ይሄንኑ ትመለከታለህ፡፡ ሜዳ ውስጥ ሲያነሳሳ በጣም ጎበዝ ነው፡፡ መልካም ባህሪ ያለው ሰው ነው፡፡ የእኛ ትወልድ ታላቅ አጥቂ ነው፡፡» በመጣበት ዓመት ምንም ዋንጫ ሳይስም ዓመቱን ቢያጠናቅቅም የቋሚ ተሰላፊነትን እድል ያገኘው ግን ወዲያው ነበር፡፡ በቀጣዩ ዓመት የጥሎ ማለፍ ዋንጫ አነሳ፡፡

**ጉዞ ወደ ድሬ፡-** በ1989 ዓ.ም. በነበረው የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ውድድር አምስተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው የቅ/ጊዮርጊስ ቡደን በ1990 ለተጀመረው የሱፐር ሊግ ውድድር የመሳተፍ እድል እንደ ሌለው ከፌዴሬሽኑ ተረዳ፡፡ «መጀመሪያ ስንት ቡድኖች እንደሚያልፉ አልነገራችሁንም፤ ሆን ተብሎ የተደረገ ደባ ነው» ሲል ክለቡ ውሳኔውን አጣጣለው፡፡ የነበራቸው እድል በአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ውድድር ላይ በመካፈል በቀጣዩ ዓመት ተጓዙሮ መጫወት ወደ ሚጠይቀውና «የኢትዮጵያ ክለቦች ካላቸው የሜዳ፣ የገንዘብ፣ የአደረጃጀት ሁኔታ ጋር የማይጣጣም» ተብሎ የሚታማው የሱፐር ሊግ (ፕሪምየር ሊግ) ለማለፍ እድላቸውን መሞከር ብቻ ሆነ፡፡ በ1990 ዓ.ም. ያለ ሽንፈት የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ዋንጫ አነሱ፡፡ ወደ ድሬዳዋ አቀኑናም ወደ ሊጉ ለመቀላቀል የሚያስችላቸውን ውድድር ሙገር ሲሚንቶንና ምድር ባቡርን አስከትለው በአሸናፊነት አጠቃቁ፡፡ በድሬው ውድድር ላይ ከጊዮርጊስ አዳጊ ቡድን የመጣው ልጅ (ሙሉዓለም ረጋሳ) መሰለፍ እንዳለበት እያጉረመረመ ነው፡፡ ተስፋዬም በሙሉዓለም ችሎታና ፀባይ እምነተ አለው፡፡ ራሱን መስዋዕት በማድረግ የዘወትር የተሰላፊነት እድሉን «ከእኔ የተሻለ ነው» በማለት ለሙሉዓለም የመሰለፍ እድል እንዲሰጠው የቡድኑ አሰልጣኝ ለነበረው አስራት ኃይሌ ይነግረዋል፡፡ አስራት ሀሳቡን ተስማምቶ ገቢራዊ ቢያደርገውም በወሳኝ ሰዓት የተስፋዬ ጥያቄ ወደ ኋላ ማፈግፈግ መስሎት ብዙ ደስተኛ አላደረገውም፡፡ ሙሉዓለም የተሻለ እንቅስቃሴ በማሳየት ቡድኑ ዋንጫ አንስቶ ፕሪምየር እንዲገባ እገዛ አደረገ፡፡ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰውም በኢትዮጵያ የጥሎ ማለፍ ሻምፒዮና በኢትዮጵያ ቡና በፍፃሜ ተሸንፈው ዋንጫ

እስካጡበት ጨዋታ ድረስ ሙሉዓለም ተስፋ ሰጪ የሆነ ብቃቱን በማሳየት የተስፋዬ ቋሚ መቀመጫ ቦታ አግዳሚ ወንበር እንዲሆን አደረገ፡፡

**ዝምታውን ማን ገፈፈው?፡-** ተስፋዬ አርጌቾ በክለብ ደረጃ ታቅፎ መጫወት ከጀመረበት ከ1981 ዓ.ም. አንስቶ በቋሚነት መጫወት ለምዷል፡፡ ጊዮርጊስ ቤትም ወደ ቋሚ አሰላለፍ መጥቶ ለመዋሀድ ባይቀለውም አልከበደውም፡፡ የተቀያሪ ተጨዋቾች መቀመጫ አግዳሚን ምናልባት ተቀይሮ ወጥቶ ሲቀመጥበት እንጂ በተቀያሪነት ከጨዋታ ጅምሬ አንስቶ ማሞቅን ብዙ አለመደም ነበር፡፡ የጥያቄው መነሻ የወንበሩን ትውውቅ አጠናከረለት፡፡ በ1991 ዓ.ም. ጊዮርጊስ ፕሪምየር ሊጉን በተቀላቀለበት ዓመት ዋንጫ ከፍ ሲያደርግ የተስፋዬ ሚና አከታትሎ እንዳነሳበትና ማራኪ ብቃቱን እንዳስመሰከረባቸው ዓመታት እጅግም አልነበሩም፡፡ የዓመቱን በርካታ ጨዋታዎች ከወንበር እየተነሳ በመግባት አሳለፈ፡፡

በተጠቀሰው ዓመት መጨረሻ ቅ/ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና ለተከታታይ ዓመት ለኢትዮጵያ ጥሎ ማለፍ ዋንጫ ፍፃሜ ይደርሳሉ፡፡ ስታዲየሙ ነፋስ ማስገቢያ እስኪያጣ በተመልካች ጥቅጥቅ ብሏል፡፡ ጊዮርጊሶች በኢትዮጵያ ቡና በጭማሪ ሰዓት የመጨረሻ ደቂቃ በተቆጠረባቸው ጎል አንድ አቻ በመውጣት በመለያ ምት ተሸንፈው የያዙት የዋንጫ ጆሮ የለቀቁበትን ያለፈውን ዓመት (1990) ታሪክ ዳግመኛ ላለመድገም ወደ ሜዳ ገቡ፡፡ በጨዋታው የመጀመሪያ 45 የመጀመሪያ ደቂቃዎች የብቃቱ ጫፍ ላይ የነበረው አሸናፊ ሲሳይ ተጐድቶ ለመውጣት ተገደደ፡፡ ከግራ ጥላ ፎቅ እስከ መሀከል ካታንጋ ድረስ ያየሉ የሳንጆርጅ ደጋፊዎች ታሪክ ሊደገም ነው በሚል ስጋት ተውጠው ፀጥ ረጭ አሉ፡፡ የአሰልጣኝ አስራት ኃይሌም ስጋት አየለ፡፡ አሸናፊን ተክቶ ወደ ሜዳ ለመግባት ከሜዳው ጥግ የቆመው በዓመቱ በብዙ ጨዋታዎች ላይ ያልታየው ተስፋዬ ኦርጌቾ መሆኑ ስጋቱን ይበልጥ አናረው፡፡ ኢትዮጵያ ቡና ቅድሚያ ጐል በማስቆጠር ጨዋታውን መምራት ጀመረ፡፡ ጊዮርጊስ ድንጋጤያቸው ጨመረ በተስፋዬ ጎል አቻ ሆኑ፡፡ መደበኛው የጨዋታ ሰዓት መሳ ለመሳ ተጠናቀቀ፡፡ በጭማሪ ሰዓት ቅድሚያ የማግባቱን እድል ቡና ወሰደ፡፡ የአጥቂ መስመር ክፍተትን ለመሙላት ከፊት የቆመው የአማካይ ስፍራ ተጨዋቹ ተስፋዬ አርጌቾ ሁለተኛ ጎል ደግሞ ቡድኑን አቻ በማድረግ ከአጥቂ በላይ ተግባሩን እንዲወጣ አደረገው፡፡ ቡድኖቹ ወደ መለያ ምት አምርተው የኢትዮጵያ ቡናው ሚካኤል ሽፈራው ያመከናት የመጨረሻ ኳስ ጊዮርጊስ አሸናፊ መሆኑን አበሰረች፡፡ የአንጋፋው ክለብ ደጋፊዎች በወሳኝ ሰዓት ትልቅ ውለታ የዋለላቸውን የወንጂው ልጅ ደስታ ዘግኖ ሰጥቷቸዋልና ሲያንቆለጳጵሱት አመሹ፡፡ ተስፋዬ ሁኔታውን ያስታውሳል፡፡ «ዓመቱን ሙሉ ተቀያሪ ተጨዋች ነበርኩ፡፡ መሰለፍ የጀመርኩት በመጨረሻዎቹ ጨዋታዎች ላይ ነበር፡፡ ጥሩም ነበርኩ፡፡ አሸናፊ አምስት ደቂቃ እንደተጫወተ ተጐዳና ወጣ፡፡ ደጋፊያችን ጐል የማግባት እድላችን የጠበበ መስሎት አሸናፊ ሲወጣ እኔ ስገባ እምነት አልነበረውም፡፡ የእኔ ሁለት ጐሎች ለአሸናፊነት ረዱን፡፡ በህይወቴ የማልረሳው መልካም የጨዋታ ቀኔ ነው፡፡»

**የጭለማ ጉዞ፡-** 1994ን ያለ ስራ አሳልፏል፡፡ የችግርን መራራ ጣዕም ለመቅመስ ቻለ፡፡ በጨዋታ ዘመኑ ያገኘው ፍቅር ተመንዝሮ የቤት ኪራይና የቀለብ ወጪ መሸፈን የሚችል ቢሆን ኖሮ

የብዙ ዓመት ወጪ ይሆን ነበር:: የጭለማ ጉዞውን ተያያዘው:: «እየተቸገርኩ ችግሬን ችዬ ኖሬያለሁ» ባዩ ተስፋዬ ጓደኞቹ እየረዱት አዲስ አበባ ውስጥ እየኖረ በ1995 የ1ኛ ደረጃ የአሰልጣኝነት ኮርስ ወሰደ:: በ1997 ሁለተኛ ደረጃ (ማሻሻያ) የአሰልጣኝነት ኮርስ በመውሰድ በ1998 የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ረዳት አሰልጣኝ በመሆን ስራ ጀመረ:: የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ለትምህርት ወደ ራሺያ ሲያቀኑም ዋና አሰልጣኝነት ሆኖ ተሾመ:: ቡድኑ በብሄራዊ ሊግ ውድድር ላይ ተካፋይ ነበር:: በ2000 ዓ.ም ደግሞ ፕሪምየር ሊጉ ላይ ከተካፈሉት 25 ቡድኖች አንዱ የተስፋዬ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ነበር:: በተጠናቀቀው ዓመት ዳግመኛ ወደ ስራ ፈትነት ብቻ ሳይሆን ከ1994-97 ድረስ ወዳጣጣመው የችግር ኑሮ ተመለሰ:: ችግር በቤት ሳይሻል አይቀርም አለና ቤተሰብዎቹጋ ወንጂ ከተመ:: ተጨማሪ ፈተና አገኘው:: በችግር ላይ በሽታ:: አምጥቶበታልና የነበረው እድል መፀለይ ብቻ ነበር:: በተጠናቀቀው ዓመት የመጨረሻ ወር ወባና ታይፎይድ በጋራ ችግር ባደከመው ሰውነት ላይ ተጨመሩ:: የህመሙ ደረጃ ከፍ በማለቱም ወንጂ ሆስፒታል ገባ:: ራሱን አያውቅም ነበር:: ማንንም ሰው ማስታወስ አቃተው፤ አጠገቡ ሆኖ ሲያስታምመው የነበረው ታናሽ ወንድሙን ታገስ ኦርጌቾንም ጭምር ረሳ:: ከአራት ቀን የወንጂ ሆስፒታል ቆይታ በኋላ ከ1984-91 ያገለገለበት የቀድሞ ክለቡ ቅ/ጊዮርጊስ አስጠርቶት ኖብል ክሊኒክ ገብቶ እንዲታከም አደረገው:: «ጓደኞቼን ሁሉ ረሳሁ:: መናገር ብቻ ሳይሆን መስማትም አቃተኝ:: ዶክተሮቹ የመድኃኒቱ ፀባይ መሆኑን ነገሩኝ::» የሚለው ተስፋዬ አሁን ጤንነቱ መለስ ብሏል:: ከሐኪም ቤት በመውጣት በስፖርት አፍቃሪው አቶ አክሊለማርያም ተስፋዬ ቤት ማረፊያ ክፍል ተሰጥቶት ህክምናውን እየተከታተለ ነው::

**ሱፐር ኤግልስን ገዳይ:-** ተስፋዬ በጊዮርጊስ ቆይታው በ1986፣ 87 እና 90 የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ሻምፒዮና ዋንጫን አንስቷል:: በ1988 ጊዮርጊስ ሻምፒዮን ቢሆንም በዓመቱ መጀመሪያ ወደ ፊንላንድ የፕሮፌሽናል የተጨዋችነት እድል አግኝቶ ሄዶ ቢመለስም የተጨዋቾች የምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ ስለሆነ የመጣው ዝርዝር ውስጥ አይካተትም:: የአውሮፓውያን ክለቦችን ትኩረት መሳብ በራሱ ቀላል ነገር አይደለም:: ከትኩረትም በላይ በፊንላንዱ ጁቫስኩላ ቡድን የሙከራ ጊዜውን በተሳካ ሁኔታ አጠናቆ እንደነበር ይናገራል:: «ኮንትራት ለመፈራረም ስንደራደር የሚከፈለኝ ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ቆይታዬ በአጭር እንዲቋጭ አድርጐታል::» ይላል በቶሎ የመመለሱ ሚስጥር ምን እንደሆነ ለአውራምባ ታይምስ ሲገልፅ:: በ1991 የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ፣ ጥሎ ማለፍ ዋንጫና የአሽ ናፊዎች አሸናፊ ዋንጫን ስሟል:: በብ/ቡድን ደረጃ በሀገርና በውጪ ሀገር የደርሶ መልስ ጨዋታዎችን ከማድረግ ውጪ ያን ያህል የሚወራ ውጤት እንደ ሀገሩ ሁሉ እሱም የለውም:: በ1983 ወጣት ቡድን፣ ከ1984-89 መጨረሻ ብ/ቡድን ውስጥ አገልግሏል:: በ1985 አሙኒኪ፣ ፊኒዲ ጆርጅና ዳንኤል አሞካቺን ያካተተውን ናይጄሪያን በአዲስ አበባ አንድ ለምንም ሀገራችን ስታሸንፍ ብቸኛዋን የድል ጐል በማስቆጠር የስታዲየሙን ድባብ በሀሴት የቃኘው ተስፋዬ አርጌቾ ነው::

**የተስፋዬ ተስፋ:-** በመከራ የተፈተነችውና እየተፈተነች ያለችው የተስፋዬ ነፍስን ለማቆየት ዘጠኝ አባላት ያሉት ኮሚቴ ተዋቅሯል:: በኮሚቴ ውስጥ ከተስፋዬ ጋር አብረው የተጫወቱ የክለብና የብ/ቡድን የቀድሞ ተጨዋቾች፣ አሰልጣኞች ተካተዋል:: ኮሚቴው እንቅስቃሴውን ጀመሯል::

መስከረም 24 በአዲስ አበባ ስታዲየም በቅ/ጊዮርጊስ፣ በኢትዮጵያ ቡናና በሰበታ ከነማ ቡድኖች መሀከል ለገቢ ማሰባሰቢያነት የሚረዳ በድምሩ 135 ደቂቃ የሚፈጅ የሦስትዮሽ ጨዋታ ለማድረግ እቅድ ነድፏል:: ቡድኖቹም ፈቃደኝነታቸውን ገልፀዋል:: ፌዴሬሽኑም በቃል ደረጃ ሜዳ የፈቀደ ሲሆን በደብዳቤ ማረጋገጥ ብቻ ይቀረዋል::

«ክለቦቹ ጥያቆያችንን ከመቀበል ባለፈም የገንዘብ እርዳታ ሊደረጉ እንደሚችሉ ነግረውናል» የሚለው የኮሚቴው ሰብሳቢ መላኩ ወ/ሰንበት «በሄድንባቸው ቦታዎች ሁሉ ጥሩ ነገር እየየን ነው:: ተስፋዬ አሁን ላለበት ደረጃ የደረሰው በሰዎች እርዳታ ነው:: በኑሮውም ሆነ በጤናው በይበልጥ እንዲሻሻል እስከዛሬ ከነበሩ የእርዳታ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች የተሻለ ነገር (ገንዘብ) ይገኛል ብለን እናስባለን» ሲል እምነቱን ገልጿል:: ከተስፋዬ የጨዋታ ዘመን ለብ/ቡድን የተሰለፉ ተጨዋቾች ለሁለት ተከፍለው በኢንስትራክተር ካሳሁን ተካና ስዩም አባተ አሰልጣኝነት (ሁለቱም ተስፋዬን በብ/ቡድን አሰልጥነወውታል::) ወደ ሜዳ ይገባሉ:: እድሜያቸው ከ40 ዓመት በላይ የሆኑ የቅ/ጊዮርጊስና የኢትዮጵያ ቡና ደጋፊዎችና አመራሮችም ጨዋታ ያደርጋሉ:: ዝግጅቱ በስፖንሰሮች የሚታጀብ ሲሆን ትልልቅ እንግዶች ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል:: «በህዝብ የሚወደድ አንድ ሰው እንደሚገኝ እርግጠኛ ነኝ» በማለት ስም ከመናገር የተቆጠበው ሰብሳቢው ነገሮች በተሳኩ መንገድ እየሄዱ መሆኑን አስታውቋል:: ታሞ በተኛበት ሊያስታምሙትና ሊጠይቁት የተመላለሱትን ሲመለከት ቅሪላ መግፋቱን ያመሰግናል:: ስላደረጉለት ሁሉ የቅ/ጊዮርጊስ ቡድንን፣ አቶ አክሊለ ማርያም ተስፋዬን ሊያቋቁሙት የተሰባሰቡትን የኮሚቴ አባላትና ስፖርት ቤተሰቡን ያመሰግናል:: ተኝቶ የነበረበት ኖብል ክሊኒክ «ጢም» ብሎ እስኪጨናነቅ ብዙ የስፖርት አፍቃሪያን ተገኝተው ጤናን ተመኝተውለታል:: መስከረም 24 ይህ ፍቅር ወደ ገንዘብ እንደሚቀየር የኮሚቴውም ሆነ የተስፋዬ ተስፋ ነው::